# 4

# መንፈስ ቅዱስ

ከሥላሴዎች ውስጥ ስለ መንፈስ ቅዱስ ያለን ግንዛቤ ያለጥርጥር በጣም ትንሽ ነው። ለማረጋገጥ ያህል የሚከተሉትን አስቸጋሪ ቃላት እንመልከት። "አካል"- ሦስት አካላት አንድ አምላክ ስንል ምን ማለታችን ነው? እንዲሁም "መንፈስ"ን እንደ አካል መግለጥ እንግዳ ነገር ይመስላል። ቢሆንም ይህን ፅንሰ አሳብ መረዳት ለብዙ ትምህርቶች፥ ለምሳሌ ለመጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃልነት፥ የደኅንነትን የተለያዩ ገጽታዎች ለማወቅና ክርስቲያናዊ አኗኗርን ለመረዳት መሠረት ነው። ስለሆነም ይህን ተገቢ ጥያቄ በማቅረብ እንጀምር።

## መንፈስ ቅዱስ አካል ነውን?

አካል የሚለውን ቃል ስናነሳ በመጀመሪያ የሚታወሰን የሰው አካል ነው። ስለዚህም አካል እንደ ሰው ሁሉ ቁሳዊ አካል፥ ነፍስና መንፈስ ያለው ነው ብለን እናስባለን። ሰውየው ሞተ ብለን እንናገራለን። እንደ እውነቱ ግን አካሉ ሞተ ማለት ነበረብን። በሌላ አነጋገር አካልን ከሰውነት ለይተን ለማየት ልምዱ ስለሌለን ግንዛቤው ያስቸግረናል። ይሁን እንጂ አንድ ሰው ሲሞት መኖር አለማቋረጡን እንዲሁም ነፍሱና መንፈሱ በመንግሥተ ሰማያት፥ ወይም በገሃነም እንደሚኖር እንናገራለን። ሰውዬው ቢሞትም ኗሪነት አለው። ለምሳሌ አባትዎ ወይም እናትዎ በጌታ ድነው ቢሞቱ ከእግዚአብሔር ጋር እንዳሉ ያውቃሉ። ስለዚህ ስለ አካል ስንናገር ከሰብአዊው ሰውነት ባሻገር ለማሰብ መቻል አለብን። መላእክት እውነተኛ ፍጥረታት ሲሆኑ፥ ሰው መሰል አካል የሌላቸው መናፍስት መሆናቸውን ግን አለመዘንጋት ነው። ሆኖም መንፈሳዊ አካል አላቸው። እንደዚሁም እግዚአብሔር መንፈስ ነው፥ ደግሞም አካል አለው። ስለዚህ መንፈስ ቅዱስም አንድ አካል ስለሆነ፥ አካል የምንላቸው ባሕርያት ሁሉ አሉት ማለት ነው። ከዚህ በመነሳት መንፈስ ቅዱስም አካል ነው ከሚለው መደምደሚያ እንደርሳለን።

### *አዎን፥ አካላዊ ባሕርይ ስላለው በእውነት አካል ነው*

አካልን አካል የሚያሰኙት ዋና ዋና ነገሮች ምንድናቸው? ሦስት ነገሮች አሉ፦ አካል እውቀትና ስሜት እንዲሁም ፈቃድ ሊኖረው ይገባል። ግዑዝ ነገር

ግን እነዚህ ባሕርያት አይኖሩትም። መንፈስ ቅዱስ ግዑዝ አይደለም፤ እውቀት፥ ስሜት፥ ፈቃድ አለው።

(1.) መንፈስ የእግዚአብሔርን ነገር ያውቃል፥ ይህ ጥበብ ነው (1ኛ ቆሮ. 2፡10-11)። በተጨማሪ "የመንፈስ አሳብ" የሚል ቃል እናነባለን (ሮሜ 8፡27)።

(2.) መንፈስን ማሳዘን ይቻላል (ኤፌ. 4፡30)፤ ግዑዝ ነገርን ማሳዘን ግን የማይታሰብ ነው።

(3.) "እንደፈቀደ" መንፈሳዊ ስጦታዎችን የሚለግስ መንፈስ ቅዱስ ነው (1ኛ ቆሮ. 12፡11)። ይህን ቃል "እንደ እርሱ ዓላማ" ብሎ መተርጎም ይቻላል። ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ አካላዊ ባሕርያት አሉት።

## *አዎን፥ እንደ አካል መሥራት ይችላል*

ምንም እንኳን መንፈስ ቅዱስ በሰዎች የሚሠሩ አያሌ ተግባራት ቢፈጽምም፥ ሥራዎቹ ሰዎች የሚያከናውኗቸው ብቻ ናቸው ማለት አይቻልም። ለምሳሌ መንፈስ ያስተምራል፥ የአካባቢ ሁኔታዎችም ያስተምራሉ። ከልምምዶች ብንማርም፥ ልምምዶች አካል አላቸው ማለት አይደለም። አካልና እስትንፋስ ባላቸው ነገሮች ብቻ የሚከናወኑ ነገሮች እንደመኖራቸው መንፈስ ቅዱስም የሚያከናውናቸው ሥራዎች አሉ። ለምሳሌ ይጸልይልናል (ሮሜ 8፡26)፥ ነገሮችና ሁኔታዎች ግን ይህን አያደርጉም። ተአምራት ያደርጋል (ሐዋ. 8፡39)፥ ይህም ግዑዛን ነገሮች የሚችሉት ተግባር አይደለም።

## *አዎን፥ መንፈስ ቅዱስ እንደ አካል መሰየሙ እውነት ነው*

መንፈስ የሚለው ቃል በግሪክ 'ኑማ' ነው። (ይህም ከነፋስ ጋር ግንኙነት ላላቸው ቃላት መሠረት ሆኖ፥ እንደ "ኑማቲክ" ወይም "ኒዩሞንያ" (የሳምባ ምች) ያሉትን ጉዳዮች ለመግለጥ ያገለግላል።) ይህ ቃል ግዑዝ ጾታ ነው። ቋሚ የሰዋስው ሕግ እንደሚያስተምረን ተውላጠ ስም በስም ምትክ የሚገባው የስምን ጾታ እንደያዘ ነው። "መንፈስ" የሚለው ቃል በተውላጠ ስም ሲተካ ግን ይህ ሕግ ሁሌ እውነት አይሆንም። ለምሳሌ በዮሐንስ 16፡13-14 ላይ "እርሱ" የሚለው ቃል በተባዕታይ ጾታ ነው የተመለከተው። እንዲሁም በኤፌሶን 1፡14 ላይ "እርሱም" ተብሎ በተባዕታይ ተውላጠ ስም ተገልጧል። እነዚህ ሁሉ ለተሳሳተ ሰዋስዋዊ አጠቃቀም ምሳሌ ቢሆኑም፥ ለጥሩ ሥነ-መለኮት ትምህርት እጅግ ጠቃሚ ናቸው። ምክንያቱም መንፈስ ግዑዝ ነገር ሳይሆን፥ አካል መሆኑን በግልጥ ያሳያሉ።

## *እምነት፥ መንፈስ ቅዱስ እንደ አካልነቱ ከሌሎች አካላት ጋር ግንኙነት አለውና*

ለምሳሌ እርስዎ የጥምቀትን ሥርዓት እንዴት በትክክል ሊገልጡት ይችላሉ? ("በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም" ማቴ. 28፡19)፥ ሲሉ ሁለቱን አካላት (አብንና ወልድን) እና አንድ ነገር (መንፈስ ቅዱስ) ማለትዎ ይሆን? ይህን ካሉ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ከጌታ ጋር ባለው ግንኙነት ሳቢያ ሁለቱም አካል መሆናቸው ተገልጧል (ዮሐ. 16፡14)። እንዲሁም የመንፈስ ቅዱስ አካልነት ከሰዎች ጋር ባደረገው ግንኙነት ተገልጧል (ሐዋ. 15፡28)።

## መንፈስ ቅዱስ አካል አይደለም የሚሉ ወገኖች አመለካከት

የመንፈስ ቅዱስን አካልነት ወይም መለኮትነት የሚክዱት ሰዎች ብዙውን ጊዜ በአንደኛው የሞዳሊዝም ዓይነት ይመደባሉ። ይህ ስሕተት በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ በተደጋጋሚ ታይቷል። "ሰቤሊያኒዝም" [Sabellianism] የተባለ ሌላ እምነት ደግሞ (215 ዓ.ም.) "እግዚአብሔር በሦስት የተለያዩ መልኮች ራሱን ቢገልጥም አንድ አምላክ ነው" የሚል ትምህርት ነበር የሚያስተምረው። ይህ የእምነት ክፍል እግዚአብሔር ራሱ ሦስት ሚና ይጫወታል በሚል ስሕተት የተነሳ የመንፈስን የተለየ አካልነት ይክዳል። እንደዚሁም ሶሲኒየስ (1539-1604 ዓ.ም.) መንፈስን "ከእግዚአብሔር ወደ ሰው የፈሰሰ ጸጋ ወይም ኃይል ነው" ብሎ ተርጉሟል። ብዙ ለዘብተኞች ከዚህ አሳብ ጋር ይስማማሉ፤ በነሱ አመለካከት መንፈስ ቅዱስ ብዙ ጊዜ ቢጠቀስም አካል ሳይሆን፥ ኃይል ወይም ተጽዕኖ ብቻ ነው። የ"ባርቲያኒዝም" [Barthianism] ተከታዮች የሞዳሊዝምን አመለካከት በመጋራታቸው ብዙ ጊዜ ይወቀሳሉ፤ ምንም ቢሆን ስለ ሥላሴዎች ያላቸው ግንዛቤ ተመሳሳይ ነው።

## መንፈስ ቅዱስ ፍጹም አምላክ ነውን?

ስለ መንፈስ ቅዱስ አካልነት የቀረበው ማረጋገጫ አምላክነቱን የሚመሰክር ሊሆን አይችልም። በአንጻሩ የሚያረጋግጠው ግን መንፈስ ቅዱስ አምላክ ከሆነ እንደ እግዚአብሔር አካል ያለው መሆኑን ነው። ብዙውን ጊዜ አካልነቱንና መለኮታዊነቱን መካድ የማይነጣጠሉ ሲሆኑ፥ አንዳንዶች ግን አካል መሆኑን ያምኑና መለኮታዊነቱን ይክዳሉ።

## አምን፥ መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ብቻ የሆኑ ባሕርያት አሉት

1. መንፈስ ሰው ጨርሶ ሊረዳ በማይቻለው አኳኋን ስለ እግዚአብሔር ያውቃል። ይህም የእግዚአብሔርን ሁሉን አዋቂነት ባሕርይ መጋራቱን ያሳያል (1ኛ ቆሮ. 2፡11-12)።

2. ሰው ከርሱ ሊሸሽ አለመቻሉ እንደ እግዚአብሔር በሁሉ ስፍራ የመገኘት ችሎታ ያለው መሆኑን ያረጋግጣል (መዝ. 139፡7)።

## አምን፥ መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ብቻ የሚቻለውን ተግባር ሊፈጸም ይችላል

እግዚአብሔር ብቻ ከሚቻለውና መንፈስ ቅዱስም ከሚፈጽማቸው (አምላክ መሆኑን ከሚያሳዩ) ተግባራት አንዳንዶቹ የሚከተሉት ናቸው:- 1. ዳግም መውለድ (ሰው ዳግም እንዲወለድ ማድረግ) (ዮሐ. 3፡5-6)፥ 2. ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንዲወለድ ማድረግ (ሉቃስ 1፡35)፥ 3. ዓለምን መፍጠር (መዝ. 104፡ 30) ጥቂቶቹ ናቸው።

## አምን፥ መንፈስ ቅዱስ ከሌሎች የሥላሴ አካላት ጋር በእኩልነት ተጠቅሷል

በብሉይ ኪዳን ከተጠቀሰው ያህዌ ጋር በአንድነት መገለጡ የመለኮታዊነቱ ጠንካራ ማረጋገጫ ነው። በብሉይ ኪዳን ያህዌ ተናግሯቸዋል የተባሉትን ቃላት አዲስ ኪዳን ሲጠቅሳቸው ተናጋሪው መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ ይገልጣል። ይህም መንፈስ ቅዱስ እንደ ያህዌ ሙሉ መለኮት መሆኑን ያረጋግጣል (ኢሳ. 6፡1-13፤ ሐዋ. 28፡25፤ ኤር. 31፡31-34፤ ዕብ. 10፡15-17)።

መንፈስ ቅዱስን መሳደብና ለመንፈስ ቅዱስ መዋሸት ለእግዚአብሔር መዋሸት እንደሆነ በአዲስ ኪዳን ተገልጧል (ማቴ. 12፡31- 32፤ ሐዋ. 5፡3-4)። መንፈስ ቅዱስ በጥምቀት ሥርዓት መጠቀሱና (ማቴ. 28፡19) በ2ኛ ቆሮንቶስ 13፡14 በሚገኘው ቡራኬ ውስጥ መገኘቱ ከሥላሴ አካላት አንዱ መሆኑን ያረጋግጣሉ።

## ስርፀት

“ስርፀት” [Procession/ፕሮሴሽን] የሥነ-መለኮት ምሁራን የመንፈስ ቅዱስንና የሌሎቹን የሥላሴ አካላት ግንኙነቶች ለመግለጥ የሚጠቀሙበት ቃል

ነው። "ስርፀት" ማለት መንፈስ ቅዱስ ከሌሎቹ የሥላሴ አካላት የበታች ወይም እኩል ያልሆነ ነበር ማለት አይደለም። ስርፀት በእግዚአብሔር ዘላለማዊ ዕቅድ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ አገልግሎቱን ይፈጽም ዘንድ በአብና በወልድ ወደ መሬት ተልኳል ማለት ነው። የዚህ አሳብ መነሻ ዮሐ. 15፡26 ሲሆን ይህም በቍስጥንጥንያ የእምነት መግለጫ ተጠቅሷል (381 ዓ.ም.)። በዚያን ዘመን አንዳንዶች የመንፈስ ቅዱስን አምላክነት በመካድ የወልድ ተከታይ ፍጡር ነው የሚል አቋም ይዘው ነበር። ይህን አቋም የያዙት ቡድኖች "መቅዶናውያን" [Macedonians] (በመሥራቻቸው መቅዶንዮስ [Macedonius] በተባለው ሰው ስም ይጠራሉ) "በመንፈስ ላይ ክፉ የሚናገሩ" የሚል ቅጽል ስም ተሰጥቷቸው ነበር። ስለዚህ ሌላ ጉባኤ ተጠራና የሚከተለውን የአቋም መግለጫ አወጣ፡- "እኛ የሁሉ ጌታ በሚሆን፣ ሕይወት በሚሰጥ፣ ከአብ በሰረፀ፣ ከአብና ከወልድ ጋር በከበረ፣ በነቢያቱ በተናገረ መንፈስ ቅዱስ እናምናለን።" ምንም እንኳ ይህ መግለጫ መንፈስ ቅዱስን አምላክ ብሎ ባይጠራ፣ ጉባኤው ስለ መንፈስ ቅዱስ የገለጣቸው ሁኔታዎች ለሌላ የሚሰጡ ስላልሆኑ፣ የመቄዶናውያኑን አሳብ የሚቃወም ነው። በ451 ዓ.ም. የተካሄደው የኬልቄዶን [Chalcedon] ጉባኤ የቍስጥንጥንያን [Constantinople] ውሳኔ በማጽናት የመንፈስ መለኮታዊነትን ትምህርተ ሃይማኖት [Doctrine/ዶክተሪን] መሠረተ።

ይሁን እንጂ፣ በ589 የተደረገው የቶሌዶ [Toledo] ጉባኤ መንፈስ ቅዱስ ከሌሎች የሥላሴ አካላት ጋር ያለውን ምስጢራዊ ግንኙነት ግልጥ የማድረጉን አስፈላጊነት አመነበትና፣ በቍስጥንጥንያ መግለጫ፣ መንፈስ ቅዱስ ከአብ የሰረፀ ነው የሚለው ቃል የወልድንና የአብን አንድነት ይክዳል ከሚል ድምዳሜ ደረሰ። ስለዚህ 'ፊሊዮክዌ' ['Filoque'] ("እና ወልድ") የሚል ታዋቂ ሐረግ ጨመረበትና "መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ የሰረፀ ነው" በማለት ወሰነ። የምዕራቧ ቤተ ክርስቲያን ከዚያ ወዲህ በወጡት የእምነት መግለጫዎቿ ይህን ሐረግ ስትጨምር፣ የምሥራቋ ቤተ ክርስቲያን ግን፣ ይህ መንፈስ ቅዱስ ሙሉ መለኮታዊ መሆኑን ይክዳል በማለት፣ ትምህርቱን መናፍቅነት አድርጋ ቆጠረችው።

የዚህ ታሪካዊ ክርክር ጠቀሜታ የጎላ ባይመስልም፣ ከጥናቱ ሂደት ስለ መለኮታዊነት፣ ስለ እኩልነት፣ ስለ ታናሽነት፣ ስለ ግንኙነት አሳብ ለማግኘትና በጉዳዮቹ ላይ ስንነጋገርም ለመጠንቀቅ ይረዳናል። ትምህርተ ሃይማኖትን በጥልቀት መከታተላችን፣ እውነትን እንድንረዳ ብቻ ሳይሆን፣ በሚገባ እንድንገልጠውም ያስችለናል። ከጥንት ከመሠረት ጀምሮ አባቶች ያደረጉትን ውይይት ማጤንም ለዚህ ይረዳል።

# የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በብሉይ ኪዳን

## የመፍጠር ድርሻው

አንዳንድ ጊዜ በብሉይ ኪዳን፥ መንፈስ የሚለው ቃል ስለ መንፈስ ቅዱስ ይናገር፥ ወይም ስለ እግዚአብሔር እስትንፋስ ግልጥ አይደለም (መዝ. 33፡6ን ይመልከቱ)። ይሁን እንጂ መንፈስ ቅዱስ በመፍጠር ውስጥ ድርሻ እንደነበረው የሚያሳዩ ጥቅሶች አሉ። አምላክ በመሆኑም፥ ሁልጊዜ በዓለም አለና መፍጠርን ጨምሮ በማናቸውም የአምላክ ሥራ ውስጥ ይሳተፋል።

የመንፈስ ሥራ የሚዛመደው በተለይ ለፍጥረት ሕይወት ከመስጠት፥ (መዝ. 104፡30፤ ኢዮብ 33፡4)፥ ሥርዓት ከማስያዝ (ኢሳ. 40፡12-13፤ ኢዮብ 26፡13)፥ የእግዚአብሔርን ክብር ከማወጅ (መዝ. 33፥6፤ ኢዮብ 26፡13) እና የማያቋርጥ እደሳና ጥበቃ ከማድረግ (ይህ በመዝሙር 104፡29-30 መሠረት ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ቢዛመድም፥ ባመዛኙ ከክርስቶስ ጋር ይያያዛል) ጋር ነው።

## በመለኮታዊ መገለጥ ውስጥ ያለው ድርሻ

በምዕራፍ 2 ከመለኮታዊ መገለጥ እና ከእስትንፋስ-እግዚአብሔር ጋር ስለተዛመዱ ነገሮች ማብራሪያ ተሰጥቷል። አሁን ደግሞ በዚህ ሥራ መንፈስ ቅዱስ በተለይ ያለውን ድርሻ እንመለከታለን።

እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን መልእክቱን ለሰዎች ለማስተላለፍ የተጠቀመው በነቢያት ሲሆን፥ መንፈስ ቅዱስ ከነቢያቱ ጋር በመሆን እግዚአብሔር ያላቸውን ብቻ እንዲያስተላልፉ ይመራቸው ነበር። ጴጥሮስ የብሉይ ኪዳንን ጸሐፊዎች በተመለከተ ሲገልጥ "በመንፈስ ተነድተው ተናገሩ" ብሏል (2ኛ ጴጥ. 1፡21)። ይህ አጠቃላይ ገለጣ በብዙ ዝርዝር ምሳሌዎች የተደገፈ ነው (2ኛ ሳሙ. 23፡2፤ ሚክ. 3፡8)። አዲስ ኪዳን፥ ብሉይ ኪዳን ውስጥ የሚገኙት አያሌ ጥቅሶች የመንፈስ ቅዱስ ምሪት ውጤቶች እንደሆኑ ያስረዳል (ማቴ. 22፡43፤ ሐዋ. 1፡16፤ 4፡25)። ጌታም በአዲስ ኪዳን ለሐዋርያቱ የገለጣቸውን ትምህርቶች መንፈስ ቅዱስ እንደሚያብራራላቸው ተስፋ ሰጥቷቸው ነበር (ዮሐ. 14፡26)። ስለዚህ መለኮታዊ መገለጥን በባለቤትነት የመራና የጠበቀ መንፈስ ቅዱስ ሲሆን፥ ሰው መሳሪያ ወይም ወኪል እንደነበረና ምንጩ ደግሞ እግዚአብሔር እንደነበር እንረዳለን።

## መንፈስ ቅዱስ ከሰው ጋር ያለው ግንኙነት

*በምርጫው (ቋሚ ባልሆነ ሁኔታ) በሰዎች ውስጥ መኖሩ።* መንፈስ ቅዱስ በብሉይ ኪዳን ዘመን በአንዳንድ ሰዎች ያድር እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስ

ይገልጣል። ስለዚህ በዚያ ዘመን በሰዎች ውስጥ የመኖሩ ጉዳይ አጠያያቂ አይደለም (ዘፍጥ. 41፡38፤ ዘኍል. 27፡18፤ ዳን. 4፡8፤ 1ኛ ጴጥ. 1፡11)። እንዲሁም አንዳንድ ጊዜ በሰዎች ላይ ይወርድ ነበር (መሳ. 3፡10፤ 1ኛ ሳሙ. 10፡9-10)። ታዲያ በመንፈስ ቅዱስ በሰው ውስጥ መሆንና ከላይ መውረድ መካከል ልዩነት አለን? ምናልባት "ከላይ መውረድ" ተመልሶ የመሄድንም ሁኔታ ያመለክት ይሆናል (መሳ. 15፡14ን ከመሳ. 16፡20 ጋር ያነጻጽሩ)። ጌታ ኢየሱስ፥ መንፈስ ቅዱስ ከብሉይ ኪዳን ሰዎች ጋር የነበረውን ግንኙነት ከበዓለ አምሳ በኋላ ከሚኖረው ጋር ባነጻጸረበት ወቅት፥ መንፈስ ቅዱስ ሁሌ ከአማኞች ጋር እንደሚኖር ተናግሯል (ዮሐ. 14:17)። ይህ ከበዓለ አምሳ በፊትና በኋላ የነበረውን ልዩነት በግልጥ ሲያመለክት፥ የብሉይ ኪዳኑም የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ተገቢ እንደነበር "መኖር" በሚለው ቃል ተረጋግጧል። መንፈስ ቅዱስ ዛሬ በአማኞች ሁሉ ውስጥ ይኖራል። ይህ ሁለንተናዊና ነባራዊ እውነት በብሉይ ኪዳን ጊዜ ቀስትና አልነበረውም።

*ለልዩ አገልግሎት ማብቃቱ።* በአንዳንድ ሥራዎች ላይ መንፈስ ቅዱስ ኃይል ሰጥቷል። ለምሳሌ፥ ከመገናኛው ድንኳን ጋር ለተያያዘ ልዩ ሥራ (ዘጸ. 31፡3) እና ለሌሎችም ታላላቅ ሥራዎች (መሳ. 14፡6፤ 1ኛ ሳሙ. 16፡13)።

*ኃጢአት ማገዱ።* ኃጢአትን ማገድ ከጥንት ጀምሮ የመንፈስ ቅዱስ ልዩ ሥራ ሲሆን (ዘፍጥ. 6፡3) ሰዎች ስሙንና ኃያልነቱን ባሰቡ ቁጥር ከኃጢአት ተግባር ይታቀባሉ (ነህ. 9፡20፤ መዝ. 51፡11)።

## የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በክርስቶስ ሕይወት

### *ከድንግል ከመወለዱ ጋር*

የሚወለደው ሕፃን ከመንፈስ ቅዱስ እንደሚፀነስ ገብርኤል ለማርያም በግልጥ አበሰራት (ሉቃስ 1፥35)፤ ለዮሴፍም ይህ እውነት በመልአክ ተነግሮታል (ማቴ. 1፡20)።

### *በሕይወቱ*

ክርስቶስ በጥምቀቱ ወቅት ልዩ በሆነ መንገድ በመንፈስ ቅዱስ ተቀብቷል (ሉቃስ 4፡18፤ ዮሐ. 1፡32)። ይህም እግዚአብሔርን ያገለግል ዘንድ ኃይል ሰጥቶታል (ሐዋ. 10፡38)። ጌታችን በመንፈስ የተሞላና የሚመራም ነበር (ሉቃስ 4፡1 እንዲሁም ዮሐ. 3፡34፤ ኢሳ. 42፡1)። በመንፈስ ኃይል ተአምራትን ያደርግም ነበር (ማቴ. 12፡28)። የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ጥገኛ መሆኑ የትሕትናውን ጥልቀት ከማመልከቱ ባሻገር፥ ይህ ድጋፍ ለኛም በጣም

አስፈላጊ መሆኑን ያሳያል። እርሱ ይህን ያህል የመንፈስ ቅዱስ እርዳታ ካስፈለገው፥ እኛስ በምን ያህል ብልጫ በመንፈስ ቅዱስ መደገፍ አለብን?

### *በሞቱና ትንሣኤው*

ዕብራውያን 9፡14 ስለ መንፈስ ቅዱስ ከተናገረ (አንዳንዶች እንደሚሉት ስለ ክርስቶስ ስለ ራሱ መንፈስ ሳይሆን) ራሱን መሥዋዕት አድርጐ ያቀረበው በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ነበር ማለት ነው። ሮሜ 1፡4 (አንዳንዶች 1ኛ ጴጥ. 3፡18ንም ይጠቅሳሉ) መንፈስ ቅዱስ በትንሣኤው የነበረውን ሥራ ያሳይ ይሆናል። ደግሞም ትእዛዛቱን ለሐዋርያቱ የተሰጡትና በነርሱም በኩል ለእኛ የተላለፉልን በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ነው (ሐዋ. 1፡2)።

## የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በደኅንነት ውስጥ

ዛሬ በጣም ጠቃሚውና ታላቁ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ፥ ደኅንነትን የሚመለከት መሆኑ አያጠያይቅም። እርግጥ ከሕሊና ወቀሳ አንስቶ ሰውን መንግሥተ ሰማይ እስከ ማስገባት ድረስ የእርሱ ሥራ ነው።

### *የሕሊና ወቀሳ (ዮሐ. 6፡8-11)*

> "የሕሊና ወቀሳ" የሚለው አሳብ ውስብስብ ነው። የሚያጠቃልላቸውም አሳቦች ሥልጣናዊ ምርመራን፥ የማያከራክር ማስረጃን፥ የማያወላውል ፍርድን፥ ቅጣትን ያካትታል። የጉዳዩ ማብቂያ ምንም ይሁን ምን በሌላው ላይ "የሚፈርድ" እውነትን በማያሻማ ሁኔታ ወደ ብርሃን በማውጣት ማሳየትና እንዲታመንበት ማድረግ ይኖርበታል። ይህን ዓይነቱን ተዓማኒ ፍርድና ውሳኔ የሚቃወም፥ እውነትን ካየም በኋላ በጭፍን የሚክድ መጥፎያውን ያከብዳል። እውነት እንደ እውነት ካልታየና ተቀባይነት ካላገኘ ፍርድን ያስከትላል።"[1]

በዚህ መንፈስ ቅዱስ የወንጌልን ብርሃን ላልዳነ ሰው በማብራት ሰውየው ኢየሱስን እንደ ግል አዳኙ ተቀበለም አልተቀበለ፥ እውነቱን እንዲያውቅ ያደርጋል። ወቀሳው መልእክቱን ግልጥ ማድረግ እንጂ፥ የማዳን (የመውለድ) ተግባር አይደለም። ማዳን ዳግመኛ ልደት መስጠት ነው። በሌላ አነጋገር ስለ እግዚአብሔር የማዳን ጸጋ የሚመሰክር ሰው ምስክርነቱ ግልጥ እንዲሆን በመንፈስ ቅዱስ መደገፍ አለበት።

የትኛውን እውነት ነው መንፈስ ቅዱስ ግልጥ የሚያደርገው? እውነቱ ስለ ኃጢአት፥ ስለ ጽድቅ፥ ስለ ፍርድ ማሳወቅ ነው (ዮሐ. 16፡8 እና ተከታዮቹ ቁጥሮች)። ሰዎች በኃጢአት ውስጥ ለመኖራቸው ማረጋገጫ ቃሉ "በእኔ

ስላላመኑ ነው” ይላል። የክርስቶስ ጽድቅ ከሞት በመነሣቱና ወደ አብ በማረጉ ተረጋግጧል። ጻድቅነቱ ወደ ሰማይ በተመለሰ ጊዜ ይፋ ሆኗል። መጪው ፍርድ የሚመሠረተውም ጥንት በሰይጣን ላይ በተፈረደው ዓይነት ይሆናል። የክርስቶስ ዋነኛ ጠላት ሰይጣን ከተፈረደበት (ዮሐ. 12፡31)፥ የእግዚአብሔርን ጸጋ የማይቀበል ሰውስ ከፍርድ ለማምለጥ ምን ተስፋ ይኖረዋል?

የመንፈስ ቅዱስ የሕሊና ወቀሳ በቅደም ተከተል የሚካሄድ ነው። ሰው በቅድሚያ ኃጢአተኛነቱን ሊያጤን ይገባል። ከዚያም ከኃጢአቱ ሊያነጻው በሚችለው ጻድቅ አዳኝ ማመን ይኖርበታል። ይህን አዳኝና ጸጋውን ካልተቀበለ ግን፥ የዘላለም ፍርድ እንደሚጠብቀው መረዳት አለበት።

## *ዳግም ልደት (ቲቶ 3፡5)*

ምንም እንኳ “ዳግም መወለድ” የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱሳችን የተጠቀሰው ሁለት ጊዜ ብቻ ቢሆን (በቲቶ 3፡5 ላይ ዳግም ልደትን የሚያሳየውና ማቴ. 19፡28 ላይ የሺህ ዓመት ግዛትን የሚያመለክተው)፥ ዳግም የመወለድ አሳብ ዮሐንስ 3ን ጨምሮ በሌሎችም ክፍሎችም ይገኛል። በክርስቶስ ለሚያምን ሁሉ ዘላለማዊ ሕይወትን የመስጠት የእግዚአብሔር ተግባር ነው። እምነትና ዳግም ልደት የተቀራረቡ ቢሆኑም፥ የተለያዩም ናቸው። እምነት የሰው ልጅ የእግዚአብሔርን ጸጋ ይቀበል ዘንድ ሊከተለው የሚገባውን መንገድና ኀላፊነት ሲያመለክት፥ ዳግም ልደት ዘላለማዊው ሕይወትን የሚያስገኝ የእግዚአብሔር ልዩ ኃይል ነው። ሁለቱም በአንድ ላይ የሚከናወኑ ስለሆኑ፥ አንዱን ከአንዱ ለማስቀደም መሞከር ፍሬ ቢስና የአእምሮ ሥራ ዓይነት ሆኖ ይቀራል። አንዳንዶች፥ ሰው በኃጢአቱና ሕግ በመጣሱ የሞተ ስለሆነ፥ ማመን አይችልም፤ ያምን ዘንድ እግዚአብሔር በቅድሚያ ዳግም ልደት ሊሰጠው ይገባል ይላሉ። ይህ እውነት ከሆነ፥ ማለት ዳግም ልደት ከተቀበለና የዘላለምን ሕይወት ካገኘ ማመኑ ለምን ያስፈልገዋል? ሁለቱ ክንውኖች በአንድ ጊዜ የሚፈጸሙና የማይለያዩ ናቸው። እንዲሁም የእግዚአብሔር ቃል ከዳግም ልደት ጋር በቅርብ የተያያዘ ሲሆን፥ ይህም ተገቢውን የትምህርት ይዘት ለሰው ልጅ እምነት ለመስጠት አስፈላጊ መገለጥ ነው (1ኛ ጴጥ. 1፡23፤ ያዕ. 1፡18)።

ምንም እንኳን ለዳግም ልደት የቅድመ ሁኔታዎች መስተካከል አስፈላጊና ጊዜ የሚፈጅ ሂደት ቢሆንም፥ ያ ታላቅ ለውጥ ያንድ አፍታ ክንውን ነው። አንድ ሰው በዚያን ቅፅበት ዳግም ይወለዳል ወይም አይወለድም። ሰውየው የሚድንበትን ትክክለኛ ጊዜ አያውቅ ይሆናል፤ ነገር ግን በእግዚአብሔር ዓይን ወይ በኃጢአቱ ሙት የሆነ ወይም በአምላክ ቤተሰብነት የተወለደ ይሆናል። ዳግም ልደት አዲስ ፍጡር ያደርጋል (2ኛ ቆሮ. 5፡17)። በጽድቅ ለማገልገል አዲስ ጉልበት ይሰጣል። ሆኖም አሮጌው ባሕርይ ሙሉ በሙሉ ይጠፋል ማለት

አይደለም። ምክንያቱም ሰው እስኪሞት ድረስ ራሱን የማገልገል ፍላጎት ይኖረዋል። ዳግም ልደት ሰውን በእግዚአብሔር ቤተሰብነት እንዲኖርና በክርስቶስ አምሳል እያደገ፥ አብን ለማስደሰት አዲስ ችሎታ እንዲኖረው ያደርገዋል እንጂ ፍጹም አያደርገውም። ከአዲሱ ባሕርይ የሚታየው ፍሬም ዳግም ልደት ለመከናወኑ እርግጠኛ ማረጋገጫ ይሆናል (1ኛ ዮሐ. 2፡29)።

## *የመንፈስ ቅዱስ በሰው ውስጥ መኖር (1ኛ ቆሮ. 6፡19)*

ዛሬ የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ልዩ የሚያደርገው የሰውየው መንፈሳዊ ሁኔታ ምንም ይምሰል ምን፥ በእያንዳንዱ አማኝ ውስጥ መኖሩ ነው። ለዚህ ቀላል መመዘኛ የሚሆነን፥ ኃጢአት የሚያደርጉ ክርስቲያኖች እንኳን መንፈስ እንደሚኖርባቸው በአዲስ ኪዳን መገለጡ ነው። የቆሮንቶስ ሰዎች ትዝ ይሉዎታል? ሥጋዊ የሆኑ አማኞች ነበሩ (1ኛ ቆሮ. 3፡3)። አንድ ወንድም (1ኛ ቆሮ. 5፡5) በከፋ ኃጢአት ተዘፍቆ ይኖር ነበር። ብዙዎቹም እርስ በርሳቸው ይካሰሱ ነበር (1ኛ ቆሮ. 6)። ይሁን እንጂ ጳውሎስ አንዳች ልዩነት ሳያደርግ በሁሉም መንፈስ ቅዱስ እንደሚኖርባቸው ጠቅሷል (1ኛ ቆሮ. 6፡19)። ይህን በመንተራስ ነው ሰውነታቸውን እንዳያረክሱ የመከራቸው። ሮሜ 8፡9 የመንፈስ ቅዱስ በአንድ ሰው ውስጥ አለመኖር ያለመዳን ምልክት ነው ይላል። ስለዚህ መንፈስ በሰው ሕይወት የሚሄድና የሚመጣ ከሆነ፥ ሰው ደኅንነት የማግኘቱና የማጣቱ ጉዳይ ይደጋገማል ማለት ነው።

እንዴት ነው አንድ አማኝ የእግዚአብሔር መንፈስ በውስጡ መኖሩን የሚያውቀው? ሁለት ማረጋገጫዎች አሉ። አንዱ የእግዚአብሔር ቃል የሚናገረውን እውነት ማመን ይሆናል። ሌላው ወደ ክርስቲያናዊ ልምምዶች ተመልክቶ የመንፈስን መኖርና በአንድ ሰው ሕይወት ውስጥ የሠራውን መረዳት ነው። ይሁን እንጂ ኃጢአት የመንፈስን ሥራ ሊያግደው ይችላልና፥ ልምምድ ሁልጊዜ የመንፈስን መኖር አያረጋግጥ ይሆናል። እናም ጤናማ በሆነ የክርስትና ሕይወት የአንድ ሰው እድገት አዝጋሚና የማይቋረጥ፥ ብሎም ልዩ የሆነ የእግዚአብሔር ኃይል የማይከሰትበት ሊሆን ይችላል። ቢሆንም ይህ ዓይነቱ እድገት የመንፈስን በአንድ ሰው ውስጥ አለመኖር የሚያሳይ ተደርጎ ሊወሰድ አይገባም። መንፈስ ቅዱስ በእያንዳንዱ አማኝ ሕይወት ውስጥ ለዘላለም ይኖራል (ዮሐ. 14፡16-17)።

## *ማጥመቅ (1ኛ ቆሮ. 12፡13)*

ጥምቀት ሲባል ብዙዎች የሚታያቸው የውኃ ምስል ወይም ልዩ የሆነ ኃይል መገለጥ ነው። ይህ ግን የመንፈስን የማጥመቅ ሥራ በትክክል አይገልጠውም። ጥምቀት የሚለው ቃል ከውኃ ጥምቀት የተለየ ነው። ይህም

ለክርስቲያን በመጀመሪያ በእግዚአብሔር ዘንድ ቦታን፣ በሁለተኛ ደረጃ ኃይልን ይሰጠዋል። ብዙ ጊዜ ሰዎች በውኃ ጥምቀትና በመንፈስ ቅዱስ ሙላት መካከል ባለው ልዩነት ግር ይሰኛሉ። ሁለቱ የተለዩ የመንፈስ አገልግሎቶች ናቸው። ከመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት መለያዎች ውስጥ የሚከተሉት ይገኙበታል።

1. የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ያለ ምንም ልዩነት ለአማኝ ሁሉ የሚፈጸም ነው። ጳውሎስ ሥጋዊ ለሆነችው የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ሲጽፍ ነበር ሁሉም በመንፈስ ተጠምቀዋል ያለው (1ኛ ቆሮንቶስ 12፡13)። ከሥጋዊነት ለመዳን ተጠመቁ ብሎ እንዳልመከራቸው ያስተውሉ።

2. የመንፈስ ጥምቀት በመጀመሪያ የተከናወነው በበዓለ አምሳ ዕለት ነበር (ጌታ በሐዋርያት ሥራ 1፡5 የሰፈረውን ቃል የተናገረው ገና ወደፊት እንደሚፈጸም አድርጎ ሲሆን፣ ጴጥሮስም በሐዋርያት ሥራ 11፡15-16 ላይ መንፈስ ቅዱስ በመጀመሪያ በበዓለ አምሳ ዕለት እንደወረደ አስታውቋል)። ስለዚህ የመንፈስ ጥምቀት ለአሁኑ ስፍረ-ዘመን ልዩ የሆነ ነገር ነው።

3. አማኝ የሚጠመቀው አንዴ ብቻ ነው (በ1ኛ ቆሮንቶስ 12፡13 ያለውና ድርጊቱ የተፈጸመበትን ጊዜ የሚያሳየው የግሥ ዓይነት [Aorist/ ኤሪስት] ጥምቀት የማይደገም መሆኑን ያሳያል)።

4. ጥምቀት አማኙን የብዙ ኃይል ምንጭ ከሆነው ክርስቶስ አካል ጋር ያዋህደዋል (ሮሜ 6፡1-10)። ይሁን እንጂ ከተለመደው ውጭ ለየት ባለ የሕይወት ልምምድ አለመኖር በመንፈስ አለመጠመቅን አያመለክትም (ይህ ከሆነማ አንድ ሰው አማኝ ቢሆንም በክርስቶስ አካል ውስጥ አልኖረም ማለት ይሆናል)። ሥጋውያኑ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች በመንፈስ ቅዱስ ተጠምቀው ነበር። የገላትያ ሰዎችም በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቁ ሆነው ከእውነተኛው ወንጌል ዞር ብለው ነበር (ገላ. 1፡6፤ 3፡27)። በልሳን ያልተናገሩ ብዙዎች ተጠምቀው ነበር (1ኛ ቆሮ. 12፡13፤ 30)። በመጠመቅ የሚገኘውን ይህን አዲስ ደረጃ ከነበረከቱ ለመለማመድ በመንፈስ ቅዱስ መሞላትን ይጠይቃል። ጥምቀቱ ለክርስትና እድገትና ልምምድ መሠረት ነው።

## ማተም (ኤፌ. 4፡30)

የአማኙ የዘላለም ደኅንነት ዋስትና ትልቁ ማረጋገጫ፣ አብ ማንኛውንም አማኝ በመንፈስ ቅዱስ ማተሙ ነው (2ኛ ቆሮ. 1፡22፤ ኤፌ. 1፡13፤ 4፡30)። ሁላችንም ታትመናል (ሥጋውያኑን የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ጨምሮ)፤ ይህም የሚሆነው ባመንን ጊዜ ነው (ኤፌ. 1፡13)።

ማተም የሚለው አሳብ ባለቤትነትን፣ ሥልጣንና ጥበቃን ያካትታል። እግዚአብሔር ስላተመን ንብረቱ ነን፤ እስከ ቤዛ ቀን ድረስ እንጠበቃለን (ከእርሱ

በላይ ኃይለኛ እስከሌለ ድረስ)። ስለ ማኅተም የሚያስረዳን ጥሩ ምሳሌ የአደራ ደብዳቤ ነው። አንድ የአደራ ደብዳቤ ፖስታ ቤት ሲመዘገብ ይታተማል። ያን የታተመ ፖስታ ሊከፍቱ የሚችሉት ላኪው፥ ወይም ተቀባዩ ብቻ ናቸው። በእኛም ሁኔታ እግዚአብሔር ላኪም ተቀባይም ነው። እርሱ ብቻ ነው ማኅተሙን ሊከፍት የሚችል። ወደ መንግሥተ ሰማያትም ሊያስገባን ቃል ገብቷል። እንግዲህ ዘላለማዊ ደኅንነት በአጭሩ ይህን ይመስላል። ነገር ግን የኤፌሶን 4፡30ን የጥቅስ አገባብ ያስተውሉ። መታተሙ መንፈስን ኃጢአት በመሥራት (በተለይም በአንደበታችን) እንዳናሳዝን ለቀረበው ወቀሳ መሠረት ነው። ስለ ዋስትና ተገቢ ግንዛቤ ማግኘት ለኃጢአት ፈቃድ ከመገዛት ይጠብቃል።

## የመንፈስ ቅዱስ ሥራ፥ በክርስቲያኑ ሕይወት

### *ስጦታን ይለግሳል*

*የመንፈሳዊ ስጦታዎች ምንጭ።* መንፈሳዊ ስጦታዎች፥ በመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ ይሰጡናል (1ኛ ቆሮ. 12፡8-11)።

*የመንፈሳዊ ስጦታዎች ትርጉም።* መንፈሳዊ ስጦታ፥ ለአገልግሎት ከእግዚአብሔር የሚሰጥ ነው። በመጀመሪያ፥ ስጦታው ችሎታ መሆኑን ካወቅን፥ ዛሬ በሰዎች አእምሮ መንፈሳዊ ስጦታን በማስመልከት ካለው ግራ መጋባት እንድናለን። ብዙ ሰዎች፥ መንፈሳዊ ስጦታ ጥቂት የታደሉ ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚያገኙት ሹመት ነው ይላሉ። ይህ ትክክለኛ አባባል አይደለም። ለምሳሌ የመጋቢነትን ስጦታ ብንመለከት፥ መጋቢው ካለው ልምድና ሥልጣን ጋር የተያያዘ ይሆናል። በትክክለኛ ትርጉሙ ካየነው ስጦታ በየትኛውም ቦታ የእረኝነት አገልግሎት የመስጠት ችሎታ ነው። ስጦታ በጂኦግራፊ ክልል ወይም በድርጅታዊ መዋቅር የሚወሰን አይደለም። ለምሳሌ ማስተማር በየትኛውም ክፍለ ዓለም፥ በክፍል ውስጥና ውጭ ሊደረግ ይችላል። ማስተማር የእግዚአብሔርን እውነት የማስተላለፍ ችሎታ ነው። እንደዚሁም ስጦታ የተለየ መስፈርት ወይም የተለየ የዕድሜ ክልል አገልግሎትን የሚጠይቅ አይደለም። የወጣቶች ሥራ ወይም የጽሑፍ ችሎታ የሚባል ስጦታ የለም። እነዚህ ሁሉ መንፈሳዊ ስጦታን ጥቅም ላይ ለማዋያ ከትምህርት ወይም ከልምድ የተገኙ ሙያዎች ወይም ተልእኮን በሥራ መተርጐሚያዎች ሲሆኑ፥ ስጦታዎች ግን ከእግዚአብሔር የተለገሱ ችሎታዎች ናቸው።

*መንፈሳዊ ስጦታዎችን ማከፋፈል።* መንፈሳዊ ስጦታዎች መንፈስ ቅዱስ እንደፈቀደ የሚለገሱ መሆናቸውን ከዚህ በፊት ተመልክተናል።

እያንዳንዱ ክርስቲያን ይብዛም ይነስ ስጦታዎች አሉት፥ ወይም ይኖሩታል (1ኛ ጴጥ. 4፡10)፤ ይህ ማለት ግን አንድ አማኝ ወይም ማኅበረ ምእመናን፥ ስጦታዎች ሁሉ አሉት ማለት አይደለም።

ከቅዱስ ቃሉ እንደሚታየው አንዳንድ ስጦታዎች ለቤተ ክርስቲያን መጀመር እንዲረዱ ብቻ የተሰጡ ናቸው። ሐዋርያትና ነቢያት የክርስቶስን አካል (ቤተ ክርስቲያንን) ለመመሥረት የተሰጡ ናቸው ይባላል (ኤፌ. 2፡20)። የመጀመሪያው የክርስቲያን ትውልድ፥ ከሁለተኛው ትውልድ ይልቅ ብዙ ድንቅ ነገሮችንና ተአምራትን ተለማምዷል (ዕብ. 2፡3-4)። ሌላው ቀርቶ የልሳን ስጦታ (በቤተ ክርስቲያን የምሥረታ ዘመን የነበረ) ከትንቢት ስጦታ ቀደም ብሎ ነበር የቀረው (1ኛ ቆሮ. 13፡8)። ይሁን እንጂ፥ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ አንድ ጊዜም ቢሆን፥ ለቤተ ክርስቲያን እስከተሰጠ ድረስ፥ ለሁሉም ቤተ ክርስቲያናት ጥቅም እንደተሰጠ ይቆጠራል።

*የስጦታዎች ዝርዝር።* የልዩ ስጦታዎች ዝርዝር በሮሜ 12፡6-8፥ በ1ኛ ቆሮንቶስ 12፡8-10፥ 28-30 እና በኤፌሶን 4፡11 ይገኛል። በዝርዝሩም ውስጥ ሐዋርያነት፥ ትንቢት፥ ተአምራት፥ ፈውስ፥ ልሳን፥ ወንጌልን መስበክ፥ እረኝነት፥ መርዳት፥ ማስተማር፥ እምነት፥ ምክር፥ መናፍስትን መለየት፥ እውቀት፥ ምሕረት፥ ቸርነት፥ ማስተዳደር፥ ተጠቅሰዋል። ይህ ዝርዝር ሙሉ ነው ብንልም፥ ምናልባት የተሟላ ሊሆንም ላይሆንም ይችላል። በመጽሐፍ ቅዱስ ያልተጠቀሰ ስጦታ ቢሆን እንኳን፥ በምንጩና በዓላማው የክርስቶስን አካል ለማነጽ የተሰጠ መሆን አለበት። ተፈጥሯዊ ችሎታን ከመንፈስ ቅዱስ ስጦታ መለየት ይገባናል። እነዚህ ስጦታዎች፥ እንደ ሙዚቃ ሞያ መንፈሳዊ ስጦታዎችን ለማከናወኛ ያገለግላሉ።

*መንፈሳዊ ስጦታን ማዳበር።* መንፈስ ቅዱስ የመንፈሳዊ ስጦታዎች ምንጭ ቢሆንም፥ ስጦታውን በማዳበር ረገድ አማኙ ድርሻ አለው። "መንፈሳዊ ስጦታን በብርቱ ተመኙ" (1ኛ ቆሮ. 12፡31) የሚለው ጥቅስ የተሻለውን ስጦታ ለማግኘት የመጣጣር ድርሻ እንዳለብን ያሳያል። ለምሳሌ የመርዳት ስጦታ ራስን በመግዛት ሊዳብር እንደሚችል ይታወቃል።

የሌሎችን አገልግሎት በመጠቀምም ስጦታዎችን ማዳበር እንችላለን (ሮሜ 1፡11 ጳውሎስ ስጦታን እለግሳለሁ ሳይል፥ በአገልግሎቱ አማካይነት መንፈሳዊ ስጦታዎቹን ለሌሎች እንደሚያካፍል ይናገራል)። ስጦታ ያላቸው ሌሎችን ሲያገለግሉ፥ ሰዎች ይታነጻሉ፥ የታነጹትም በተራቸው ያገለግላሉ፥ እነዚህም ሊያንጿቸው የሚችሉትን ያገለግላሉ፥ ወዘተ። ይህ የማያቋርጥ ኡደት ይሆናል። በዚህ መንገድ ነው የክርስቶስ አካል በብዛትም በዓይነትም ሊያድግ የሚችለው።

*ስጦታን ማወቅ።* አንድ ሰው ስጦታውን እንዴት ሊያውቅ ይችላል? ይህን በተመለከተ ሦስት አሳቦች አሉ፦ አንደኛው፥ ያሉትን መንፈሳዊ ስጦታዎች ማወቅ ነው። ለምሳሌ፥ ምሕረትን ማድረግ መንፈሳዊ ስጦታ መሆኑን የማያውቅ ሰው ይኖር ይሆናል። ይህ ግን ብዙዎች ሊጠቀሙበት የሚቻላቸው ስጦታ ነው። ስለዚህ በሕይወትዎ ያለውን ስጦታ ወደ ብርሃንና ወደ ጥቅም ሊያመጣው ይችላልና የእግዚአብሔርን ችሎታና እቅድ አይወስኑት። ሁለተኛ፥ ማንኛውንም ነገር ለጌታ ለማድረግ ፈቃደኛ ይሁኑ። ብዙ ክርስቲያኖች በቤተ ክርስቲያን ያላቸውን የዘወትር ሥራ ችላ ስለሚሉ ስጦታቸውን ሁሉ ለመጠቀም አይችሉም። ሦስተኛ፥ በአንድ ስጦታ መጠቀም ሌላውን ለማግኘት ይረዳልና ንቁ ይሁኑ! በአዲስ ኪዳን ፊልጶስን በመጀመሪያ ስናየው የመርዳት ስጦታ ነበረው (ሐዋ. 6፡5)፤ በዚህ ታማኝ ስለነበር እግዚአብሔር ወንጌልን የመስበክ ስጦታ ጨመረለት (ሐዋ. 8፡5)። ያለንን በታማኝነት ከተጠቀምንበት፥ ስፋ ዕድልና አብሮት የሚሄድ ስጦታ ይጨመርልናል።

## *መንፈስ ቅዱስ ይሞላል*

ከየዕለቱ ጠቃሚ ክርስቲያናዊ ልምምዳችን በመነሳት፥ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ያለጥርጥር የዚህ ትምህርት ዋና ክፍል ነው እንላለን። ይህ ለእውነተኛ መንፈሳዊነት፥ ለእድገትና ብስለት መነሻ ነው።

*የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ምንድነው?* የመንፈስ ሙላት ትክክለኛ ትርጉም፦ በኤፌሶን 5፡18 "መንፈስ ይሙላባችሁ እንጂ በወይን ጠጅ አትስከሩ ይህ ማባከን ነውና" በሚለው ጥቅስ ውስጥ ይገኛል። በስካርና በመንፈስ ቅዱስ ሙላት መካከል ያለው ንጽጽር መሠረታዊ ፍንጭ ይሰጣል። ይሄውም ቁጥጥር የሚለው ነው። ሰካራምና መንፈሳዊ ሰው ሁለቱም በቁጥጥር ሥር የዋሉ ሲሆኑ፥ ይህም በመጠጥ ወይም በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ሥር ናቸው ማለት ነው። ሁለቱም ከባሕርያቸው ውጭ የሆኑ ተግባራት ይፈጽማሉ። ጉዳዩን በሌላ አቅጣጫ ስንመለከተው፥ ሁለቱም ራሳቸውን መቆጣጠር ባለመቻል ለመጠጥ ወይም ለመንፈስ ቅዱስ ተገዢ ሆነዋል ማለት ነው። ይሁን እንጂ በመንፈስ የተሞላ ሰው እንደ ሰካራሙ ግልፍተኛ ወይም ወፈፌ ሳይሆን፥ በመንፈስ ቅዱስ የሚገዛና የሚመራ ይሆናል።

ደግሞም "ተሞሉ" የሚለው ቃል ትእዛዝ እንጂ የምርጫ ጉዳይ እንዳልሆነ ያስተውሉ። አማኞች ሁሉ ያለአንዳች ልዩነት መሞላት አለባቸው። በመንፈስ መሞላት ለጥቂት የተመረጡ ሰዎች ብቻ ሳይሆን፥ ለጤናማ የክርስቲያናዊ ሕይወት ሁሉ እጅግ አስፈላጊ ነው።

*አንድ ሰው በምን ያህል የጊዜ ልዩነት ነው በመንፈስ መሞላት ያለበት?* በኤፌሶን 5፡18 ላይ ያለውና “ተሞሉ” የሚለው ግስ ጥያቄውን ይመልስልናል። ግሱ የአሁን ጊዜ መሆኑ የሚያመለክተው መሞላት በተደጋጋሚ ሊለማመዱት የሚገባ ጉዳይ መሆኑን ነው። ስለዚህም “ሳታቋርጡ ተሞሉ” በማለት ቢተረጎም የሚሻል ይሆናል። በሌላ አነጋገር አንድ ክርስቲያን ይሞላ፥ አሁንም ይሞላ፥ ደግሞም ይሞላ ይሆናል። ይህ ልምምድ በቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያዎቹ ወራት በሐዋርያት ዘንድ ታይቷል። በበዓለ አምሳ ዕለት ተሞልተው ነበር (ሐዋ. 2፡4)፤ ከጥቂት ጊዜ በኋላ እነዚሁ ሰዎች ሲጸልዩ አሁንም ተሞሉ (ሐዋ. 4፡31)። ሐዋርያት ለሁለተኛ ጊዜ የተሞሉት በሕይወታቸው ኃጢአት ስለተገኘ ሳይሆን፥ ያኔ ለገጠማቸው አዲስ ሁኔታ (ለመመስከር ድፍረት እንዲያገኙ)፥ አዲስም ችግር ስለገጠማቸው (እንዳይናገሩ በሽማግሌዎች ስለተከለከሉ) መሆኑን ማስተዋል ያስፈልጋል። በአጭሩ በተደጋጋሚ መሞላት አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም በመንፈስ ቁጥጥር ሥር ሊውሉ የሚገባቸው ያልታሰቡ የሕይወት ገጠመኞች ይኖራሉና። አንድ ክርስቲያን በሚሠራው ኃጢአት መጠን (ከራስ ወዳድነት የተነሳ) የመንፈስ መቆጣጠር እየከዳው እንዳይሄድ በተደጋጋሚ መሞላት የግድ ያስፈልገዋል።

*ለመሞላት የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች ምንድን ናቸው?* ብዙ ክርስቲያኖች መሞላት በጸሎት ወይም በመናዘዝ ብዛት የሚገኝ ይመስላቸዋል። ነገር ግን አዲስ ኪዳን ውስጥ አማኞች ከበዓለ አምሳ ዕለት በኋላ ለመንፈስ ቅዱስ ሙላት ጸልየዋል የሚል ምሳሌ አናገኝም። ለዚህ ትንሽ ቀረብ የሚለው ጳውሎስ ለኤፌሶን አማኞች መጸለዩ ሲሆን (ኤፌ. 1፡ 17)፥ ይህም ቢሆን ለመሞላት የተደረገ ጸሎት አልነበረም። ምንም እንኳን ለመንፈስ ቅዱስ ሙላት በጸሎት ጊዜ ማሳለፍ ወይም መቃተት አያሻም ብንል መፈጸም ያለባቸው ሁኔታዎች ግን አሉ።

በመንፈስ መሞላት በቁጥጥር ሥር መዋል ማለት ከሆነ፥ ራስን ለእግዚአብሔር አሳልፎ መስጠትንና ለእርሱ መገዛትን ይጠይቃል። ስለዚህ ቅድመ ሁኔታው ራስን ለመሥዋዕትነት ማዘጋጀት ነው። ይህም አንድ ሰው ራሱን ለእግዚአብሔር አሳልፎ ለመስጠትና ለፈቃዱ ለመገዛት ፈቃደኛ መሆን አለበት። ምንም እንኳን ራስን ለመስጠት በመጀመሪያ ቃል ኪዳን የተገባው በአንድ ችግር የተነሳ ቢሆን፥ ይህ አንድን ነገር ለማድረግ ወይም ላለማድረግ ከሚወሰድ ውሳኔ የተለየ ነው። ራስን መስጠት፥ ሕይወቴን የሚመራት ማን ነው? ለሚለው ጥያቄ ፍጹም የሆነ መልስ ማግኘት ነው።

ቢሆንም ሁሌ ራስን ለእግዚአብሔር መስጠትና ፈቃዱን መፈጸምን ይጠይቃል። ጥያቄዎች ሲነሱም ትክክለኛውን ውሳኔ እንድናደርግ መንፈስ ቅዱስ

ይመራናል (ሮሜ 8፡14)፤ ይህን የሚፈጽምልን ከእርሱ ጋር ካለን ቅርበት የተነሳ በመሆኑ ምን ማድረግ እንዳለብን ሊነግረን አያመነታም። ራሱን የሰጠ ሰው የእግዚአብሔርን ፈቃድ መፈጸም ወይም አለመፈጸም የሚል ክርክር አይገጥምም። ከዚያ ይልቅ አደርገው ዘንድ የእግዚአብሔር ፈቃድ ምንድን ነው? በማለት ራሱን ይጠይቃል።

ሁለተኛ፡- በመንፈስ መሞላት መንፈስን አለማሳዘንን ይጨምራል (ኤፌ. 4፡30)። መንፈስን የሚያሳዝነው ምንድነው? መልሱ ኃጢአት፣ በተለይ የአንደበት ኃጢአት ነው። በጥቅሱ ውስጥ ከአፋችሁ ክፉ ነገር አይውጣ ሲል ደጋግሞ ተናግሯል።

ሦስተኛ፡- በመንፈስ የተሞላ ሕይወት፣ የመታመን ሕይወት ነው (ገላ. 5፡16)። ለምሳሌ መራመድን ብንመለከት የማያቋርጥ የመታመን ድርጊት ነው። አንድ እግራችንን አንስተን ከሌላኛው ፊት በማስቀደም ነው ጉዞ የምንጀምረው፤ ሌላው እግር ሙሉ ክብደታችንን እንደሚሸከምልን በመተማመን። እያንዳንዱም እግር ሌላው በሚንቀሳቀስበት ጊዜ በየተራ ድጋፍ ይሆናል። እግሮቻችንን እስካልተማመንባቸው ድረስ ባለንበት ቆመን እንቀራለን። ወደፊት መራመድ የሚቻለው በእምነት ብቻ ነው። የክርስትና ሕይወትም እንደዚሁ ነው። እድገት የሚኖረን በመንፈስ ቅዱስ ስንታመንና ሙሉ በሙሉ እንዲቆጣጠረን ስንፈቅድለት ነው።

በመንፈስ መሞላት በመንፈስ ቁጥጥር ሥር መሆን ማለት ሲሆን፣ ይህም ሕይወትን ለእርሱ ማስገዛት፣ ኃጢአትን ማስወገድና በእርሱ ኃይል ያለማቋረጥ መታመን ነው። ጸሎትና ቁርጥ ውሳኔ እነዚህን ሁኔታዎች ለማሟላት ያግዙ ይሆናል። ሁለቱ እንደተሟሉ የመንፈስ ቁጥጥር ወዲያው ስለሚተካ መሞላትን መለማመድ ይቻላል።

*የመሞላት ውጤቶች ምንድናቸው?* በመንፈስ የተሞላ ሕይወት ቢያንስ አራት ውጤቶች፣ ወይም በመንፈስ የመሞላት ማስረጃዎች ይታዩበታል። የመጀመሪያው፡- ከመንፈስ ፍሬዎች አንዱ ሲሆን፣ ይኸውም ክርስቶስን መምሰል ነው (ይህ ጉዳይ ከመንፈስ ሙላት ጋር ተያይዞ በገላትያ 5 ላይ ይገኛል)።

ሁለተኛው፡- አምልኮና ውዳሴ ሲሆን፣ ስለ ሙላት ዋና ከሆነው ጥቅስ በኋላ (ኤፌ. 5፡18) የመሞላት ውጤት የሆኑት ዝማሬና ምስጋና ይከተላሉ።

ሦስተኛው፡- ታዛዥነት ነው (ኤፌ. 5፡21)። በመንፈስ ቁጥጥር ሥር መሆን በባልና ሚስት፣ በወላጅና በልጆች፣ በአሠሪና ሠራተኛ፣ መካከል ያለውን

ግንኙነት ሁሉ ሰላማዊ ያደርገዋል። ይህን ጤናማ ግንኙነት የሚያናጋ ነገር ቢኖር በራስ መገዛት ነው።

አራተኛው፦ የመሞላት ውጤት ለጌታ አገልግሎት መስጠት ነው። ምን ዓይነት አገልግሎት? አጠቃላይ መልሱ በመንፈስ ኃይል የመንፈስ ስጦታዎችን በመጠቀም የሚታይ አገልግሎት የሚል ይሆናል። በተለይ ግን በመንፈስ የመሞላት ውጤቱ ብዙዎችን ለደኅንነት ወደ ጌታ ማቅረብ ይሆናል። በሐዋርያት ሥራ እንዳየነው ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ሲሞሉ የተረጋገጠው ጉዳይም ይህ ነው (ሐዋ. 2፡4ን ከ2፡41 ጋር ፤4፡8ንና 31ን ከ5፡14 ጋር፤ 6፡3ን ከ6፡7 እና 11፡24 ጋር እያነጻጸሩ ይመልከቱ)።

*ለመሆኑ በመንፈስ ተሞልቻለሁ ማለት ይቻላል?* የጉባኤው መሪ በመንፈስ ተሞላን የምትሉ እስቲ እጃችሁን አንሱ የሚልበት ስብሰባ ተካፍለው ከሆነ፥ ምናልባት ብዙዎች እጃቸውን ለማንሳት ሲያመነቱ ተመልክተው ይሆናል። አንዳንዴ ተናጋሪው ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላት ፈቃደኛ እንዲሆኑ፥ ከዚያም ተነስተው በመንፈስ ቅዱስ መሞላታቸውን እንዲያሳውቁ ግፊት ያደርጋል። የትኛው ነው ትክክል? የብዙዎች ወደ ኋላ ማለት፥ ወይስ የአንዳንዶች ድፍረት? ሁለቱም እንደ ሁኔታው ልክ ሊሆኑ ይችላሉ። በአንድ በኩል አንድ ሰው ራሱን ለመንፈስ ቁጥጥር አሳልፎ ሲሰጥ፥ መንፈስ ይሞላዋል። በሌላ በኩል ማንም ሙሉ በሙሉ በመንፈስ ቁጥጥር ሥር ያልዋለ መሆኑንና ሁልጊዜም በሕይወቱ ውስጥ በመንፈስ ቁጥጥር ሥር ሊውሉ የሚገባቸው ተጨማሪ ነገሮች መኖራቸውን መገንዘቡ አንድን ሰው ጥርጣሬ ላይ ይጥለዋል። ስለዚህ አንድ ሰው በመንፈስ ቅዱስ እንደተሞላ ቢያውቅም፥ ነገ ደግሞ ተጨማሪ መሞላት እንደሚያሻው ይገነዘባል።

## መንፈስ ቅዱስ ያስተምራል

ጌታ ከመሰቀሉ በፊት ለደቀ መዛሙርቱ ከሰጣቸው የመጨረሻ ተስፋዎች አንዱ፥ ያኔ ሊገነዘቧቸው የማይችላቸውን ብዙ ነገሮች በኋላ መንፈስ ቅዱስ እንደሚያስተምራቸው የሚያረጋግጥ ነበር (ዮሐ. 16፡12-15)። ይህ "እውነትን ሁሉ" የሚያቅፍ የመንፈስ አገልግሎት ስለ ክርስቶስ መገለጥ ያስተምራል (እንደ ግሪኩ ጥቅስ ከሆነ)። ጴጥሮስ በበዓለ አምሳ ዕለት የኢየሱስን ጌትነትና መሢህነት መረዳቱ፥ መንፈስ ቅዱስ ይህን እውነት እንዳስተማረው ያመለክታል (ሐዋ.2፡36)። በአሁኑ ጊዜ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ያለን መረጃ ሁሉ ከመጽሐፍ ቅዱስ ስለሆነ፥ በቃሉ ውስጥ ያለውን ምስጢር መንፈስ ቅዱስ ለአማኙ ይገልጥለታል። ይህ ትንቢትንም (ወደፊት የሚሆነውን ነገር) የሚያጠቃልል ነው።

እንዴት ነው መንፈስ አማኞችን የሚያስተምራቸው? ብዙውን ጊዜ የማስተማር ስጦታ ባላቸው አማኞች ይጠቀማል። ይህም በተለያዩ የማስተማር ዘዴዎች በመገልገል የሚከናወን ሊሆን ይችላል። በሌላ አነጋገር መንፈስ ቅዱስ ሰውን ለማስተማር በቃል፥ ወይም በየትኛውም የቤተ ክርስቲያን ዘመን በተጻፈ ጽሑፍ ይጠቀማል። ዮሐንስ በ1ኛ ዮሐንስ 2፡27 የገለጠው የሰው አስተማሪነት አስፈላጊ አለመሆኑን ሳይሆን፥ ያን ጊዜ በመካከላቸው ስለነበሩት ፀረ-ክርስቶሶች ቀደም ሲል ካስተማራቸው እውነት ሌላ ማንም እንደማይነግራቸውና መንፈስ ቅዱስ ብቻ እውነቱን በቀጥታ እንደሚያረጋግጥላቸው ነበር።

## መንፈስ ቅዱስ ይመራል

በሮሜ 8፡14 የተገለጠውና የመንፈስ ቅዱስ አንዱ ተግባር አማኞችን መምራት ሲሆን፥ ይህም በሐዋርያት ሥራ ውስጥ በሚገባ ተብራርቷል (ሐዋ. 8፡29፥ 10፡19-20፥ 13፡2፥ 4፥ 16፡6-7፥ 20፡22-23)። መንፈስ ቅዱስ ከእግዚአብሔር ቃል ውጭ በሆነ ሁኔታ በፍጹም አይመራም። ቃሉ ነው መሠረቱ። እግዚአብሔር እንዴት እንደሚመራን የሚነግረንም መጽሐፍ ቅዱስ ነው። መንፈስ ቅዱስ በተለያዩ ሁኔታዎች ይጠቀም ወይም አይጠቀም ይሆናል። ያም ሆነ ይህ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ፥ መንፈስ ቅዱስ የምናደርገውን ይመራን ዘንድ ከጌታ ጋር በቅርብ በመሆን መጓዝ ማለት ነው።

## መንፈስ ቅዱስ መተማመኛ ይሰጣል

መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያረጋግጥልናል (ሮሜ 8፡16)። ይህም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር የእግዚአብሔር ወራሾች ያደርገናል። የክርስቲያን እምነት ማጠናከሪያ፥ ያለጥርጥር እግዚአብሔር አንድን ሰው ለማዳን ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚፈጽማቸውን ነገሮች ከማስተዋል ነው። ስለዚህ የመንፈስ ቅዱስ ማስተማመኛ ማስተማርንም ይጨምራል። ለምሳሌ በመንፈስ ስለመቃተቱም እና መንፈስ የደኅንነታችን ፍጻሜ መያዣ እንደሆነ እየተረዳን ስንሄድ፥ እምነታችን የጸና ይሆናል። እንዲሁም ሕያው ከሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ አካል ጋር አንድ መሆናችንን ያለጥርጥር እንረዳለን።

## ይጸልያል

መንፈስ ቅዱስ በጸሎታችን ውስጥ በሁለት መንገድ ይሳተፋል። በመጀመሪያ ወደ እግዚአብሔር የምናቀርባቸው ልመናዎች እንደ ፈቃዱ መጠን ይሆኑ ዘንድ ይመራናል፥ ያሳየናል (ኤፌ. 6፡19)። ሁለተኛ "በማይነገር መቃተት" (ሮሜ 8፡26) ስለ እኛ ይጸልያል። ውጤቱ ግልጥ ባይሆንም፥ የጸሎቱ እውነተኛነት ግን የታመነ ነው። መንፈስ ይረዳናል ይላል ጥቅሱ፥ ይህም

በምናደርገው ጸሎት ከኛ ጋር ይለምናል ማለት ነው። መቃተት አለመናገርን ስለሚያመለክት ለመግለጥ ያስቸግራል። ነገር ግን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ ጸሎት የሚቀርብበት አንዱ መንገድ ነው።

# የመንፈስ ቅዱስ የወደፊት ሥራ

## *በፍዳው ዘመን*

ቤተ ክርስቲያን ከፍዳ ዘመን በፊት ትነጠቃለች የሚለውን አመለካከት ስንቀበል፥ በእግዚአብሔር መቅደስ፥ ማለት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያደረው መንፈስ ቅዱስ ይገለላል ማለት ነው። ይህ ማለት ግን ሥራውን ያቋርጣል ማለት አይደለም። በነዚያ የፍዳ ቀናት የሚድኑ እልፍ አእላፋት ሰዎች ይኖራሉ (ራእይ 7፥14)። ዳግም መወለድን የሚያገኙት በመንፈስ ቅዱስ በኩል ይሆናል። በፍዳው ዘመን መጨረሻ በሕይወት የሚገኙ እስራኤላውያን አዳኛቸውን የሚያውቁት በመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ነው (ዘካ. 12፥10)።

መንፈስ ቅዱስ በዚያን ዘመን በሚኖሩ አማኞች መካከል ስለሚያከናውነው ተግባር በግልጥ የተጠቀሰው ጥቂት ነው። አገልግሎቱ ልክ በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበረውን ከመሰለ፥ ለሰዎች ልዩ የአገልግሎት ኃይል ለመስጠት ያድርባቸው ይሆናል። ኢዩኤል 2 በሐዋርያት ሥራ 2 ይጠቀስ እንጂ በበዓለ አምሳ ዕለት ሙሉ በሙሉ እንዳልተፈጸመ ይታወቃል። ስለሆነም ፍጻሜው የፍዳን ዘመን ይጠብቃል። ምክንያቱም ጥቅሱ የመንፈስ ቅዱስን መፍሰስ ከፀሐይ ወደ ጨለማ፥ ከጨረቃም ወደ ደም መለወጥ ጋር ያያይዘዋል። እነዚህ ድርጊቶች ደግሞ በፍዳው ዘመን ማብቂያና ልክ ከክርስቶስ ዳግም ምጽአት በፊት ይከናወናሉ (ማቴ. 24፥29-30)። በተጨማሪም (ራእይ 11፥3-4) ላይ የተጠቀሱት የሁለቱ ምስክሮች አገልግሎት በፍዳ ዘመን ከሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ጋር የሚዛመድ መሆኑን ያስተውሉ (ዘካ. 4፥6)።

## *በሺህ ዓመቱ አገዛዝ*

በሺህ ዓመት መንግሥት ዘመን እስራኤል እንደምትድንና መንፈስም በሕዝቦቿ ሕይወት እንደሚኖር "በአዲስ ቃል ኪዳን" ተስፋ ተሰጥቷታል (ኤር. 31፥31-34፤ ሕዝ. 36፥27)። በዚያን ጊዜ በንጉሡ በክርስቶስ ላይም መንፈስ ቅዱስ በሙላት እንደሚኖርበት ተረጋግጧል (ኢሳ. 11፥2-3)። ያኔ ከአዳም ጀምሮ ያልታየ የእግዚአብሔር ኃይልና ሕልውና ይሰፍናል። ምንም እንኳን የዚያን ጊዜው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ የተብራራ ባይሆን፥ አገልግሎቱ ከሌሎቹ አካላት ጋር በስፋት መገለጡ ይቀጥላል።

# 5

# የመላእክት ዓለም

## (ሰይጣንና ጭፍራዎቹ የሆኑ አጋንንትን ጨምሮ)

የመላእክት ዓለም ካለፉት ዘመናት ይልቅ በአሁኑ ጊዜ ይበልጥ ይታመናል። ስለ ሰይጣን ቤተ አምልኮዎች በሰፊው ይነገራል። እንደዚሁም የታወቁ መጽሔቶች ሳይቀሩ ስለ አጋንንት ሥራዎች በብዛት ይጽፋሉ። በዚህም የተነሳ ሕዝቦች የመናፍስትን ዓለም መኖር ወደማመኑ፥ ያም ባይሆን ሊኖር ይችላል ወደማለቱ አድልተዋል።

### ስለ መላእክት ትምህርት

*መላእክት በእርግጥ አሉ?*

ማንም መላእክት የሉም ብሎ ሊያረጋግጥ አይችልም። በዓለማት ስለሚኖሩ ፍጥረታት ሙሉ እውቀት አለኝ የሚል ሰውም ፈጽሞ ማግኘት አይቻልም። አንድ ሰው ማለት የሚችለው ነገር ቢኖር፥ በእውቀቱ ከደረሰበት በመነሳት መላእክት እንዳሉ አላምንም ማለት ብቻ ይሆናል። ብዙ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ ከሚገልጠው ሌላ የፍጥረታት ሥርዓት መኖሩን ይቀበላሉ። አንድ ሰው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሰፈሩትን ማስረጃዎች ከተቀበለ፥ ስለ መላእክት መኖር ለማመን ችግር አይኖርበትም። በእርግጥ ማስረጃዎቹ ጠንካራ ናቸው።

በመጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ክፍሎች ስለ መላእክት የሚገልጥ ትምህርት ይገኛል። ትምህርቱ በአንድ መጽሐፍ፥ በአንድ ጸሐፊ፥ ወይም በአንድ ዘመን የተወሰነ አይደለም። ስለ መላእክት መኖር ቢያንስ በሰላሳ አራት የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት ተገልጧል። በተጨማሪም አስፈላጊ ባልሆነባቸው ጊዜ እንኳን ጌታችን ስለ መላእክት መኖር አንስቶ ተናግሯል። አንዳንዶች ጌታ ስለ መላእክት፥ አጋንንት እና ሰይጣን የተናገረው በጊዜው በነበሩ ያልተማሩ ሰዎች ዘንድ ለመከበርና ለመፈራት ሲል ነበር ይላሉ። በሌላ አነጋገር ስለ መናፍስት

በሚናገርበት ጊዜ ለመታየት ያህል እንዳደረገው ይቆጥሩታል። የእርሱ ዓላማ ግን ይህ አልነበረም። ያም ሆነ ይህ፥ ማንም ቢሆን ከዚህ የሚረዳው፥ ጌታ ራሱ የመናፍስቱን መኖር ማመኑን ነው (ማቴ. 18፡10፥ 26፡53)።

## *መላእክት ምን ይመስላሉ?*

መላእክት አካል* ያላቸው ፍጥረታት ናቸው። እውቀትም አላቸው (1ኛ ጴጥ. 1፡12)፥ ስሜት አላቸው (ሉቃስ 2፡13)፥ ፈቃድ አላቸው (ይሁዳ 6)። መላእክት እንደ እግዚአብሔር ባይሆኑም መንፈሳዊ ፍጥረታት ናቸው (ዕብ. 1፡14)። መላእክት አካል ስላላቸው ውሱኖች ቢሆኑም፥ ውሱንነታቸው ግን እንደ ሰው አይደለም። ዘርን የመተካት ተፈጥሮ የላቸውም) ማለት አይዋለዱም (ማር. 12፡25)፥ አይሞቱም (ሉቃስ 20፡36)፥ የሚጠሩት በተባዕታይ ጾታ ነው (ዘፍጥ. 18፡1-2 ምናልባት ከዘካርያስ 5፡9 በስተቀር)። ክንፍ አላቸው (ኢሳ. 6፡2)፥ ብዛታቸው ተቆጥሮ የሚያልቅ አይደለም (ዕብ. 12፡22)።

በጣም አስደናቂ ባሕርያቸው ግን የተደራጁ መሆናቸው ነው። ሊቀ መላእክት ተብሎ የሚጠራው ሚካኤል ብቻ ሲሆን (ይሁዳ 9)፥ ሌሎችም ይኖሩ ይሆናል (ዳን. 10፡13 ከዋናቹ አለቆች አንዱ ብሎ ስለሚጠራው)። በነዚህ ከፍተኛ ገዥዎች ሥር ሌላ የመላእክት ግዛት ክፍፍል ያለ ይመስላል (ኤፌ. 3፡10)። አማኞች ጠባቂ መላእክት እንዳላቸው ይገመታል (ዕብ. 1፡14)፥ ሕፃናትም እንዲሁ (ማቴ. 8፡10)። የአንዳንድ መላእክት ('ሱራፌል') ልዩ ሥራ እግዚአብሔርን ማምለክ ነው (ኢሳ. 6፡1-3)። የሌሎቹ ደግሞ ('ኪሩቤል') ቅድስናውን መጠበቅ ነው (ዘፍጥ. 3፡22-24)። እዚህ ላይ አንድ ጠቃሚ ነጥብ አለ። ይኸውም መላእክት የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማገልገል የተደራጁ ከሆኑ፥ የእግዚአብሔር ሰዎችም ለዚሁ ዓላማ መደራጀት ይገባቸዋል የሚል ነው።

## *መላእክት ምን ያደርጋሉ?*

መላእክት ለተለያዩ ግለሰቦችም ሆነ ቡድኖች የሚሰጡት አገልግሎት ግልጥና የማያሻማ ነው።

*ለክርስቶስ የሰጡት አገልግሎት።* በጌታችን ሕይወት ዘመን የታየው የመላእክት እንቅስቃሴ አያሌ ነበር። ለምሳሌ መወለዱን አመልክተዋል (ሉቃስ 1፡26-33)፤ መወለዱን አብስረዋል (ሉቃስ 2፡13)፤ በሕፃንነቱ ጠብቀውታል (ማቴ. 2፡13)፤ ከፈተናው በኋላ አገልግለውታል (ማቴ. 4፡11)፤ ከጠላቶቹ ሊከላከሉት ተዘጋጅተው ነበር (እርሱ አልጠራቸውም እንጂ ማቴ. 26፡53)፤

* ስለ አካል ትርጉም በምዕራፍ አራት መጀመሪያ ላይ ያለውን ማብራሪያ ይመልከቱ።

በጌቴሴማኒ አበርትተውታል (ሉቃስ 22፡43)፤ ድንጋዩን ከመቃብሩ አፍ በማንከባለል ትንሣኤውን አውጀዋል (ማቴ. 28፡2፥ 6)።

*ለአማኞች የሚሰጡት አገልግሎት።* በአጠቃላይ አማኞችን ይረዳሉ (ዕብ. 1፡14)። ይህ በተለይ ጸሎትን በመመለስ ተግባር መሳተፋቸውን ይጨምራል (ሐዋ. 12፡7)። በአደጋ ጊዜ ሲያበረታቷቸው (ሐዋ. 27፡23-24)፥ አማኞች በሚሞቱበትም ጊዜ እንክብካቤ ያደርጉላቸዋል (ሉቃስ 16፡22፤ ይሁዳ 9)። አማኞችም የደኅንነትን ትርጉም በሕይወታቸው በማሳየት መላእክትን ያገለግላሉ (1ኛ ቆሮ. 4፡9፤ ሉቃስ 15፡10)።

*ለዓለም አገሮች የሚሰጡት አገልግሎት።* ሚካኤል ሊቀ መላእክት መሆኑን አይተናል። በተለይም የእስራኤል ጠባቂ መሆኑም ተነግሯል (ዳን. 12፡1)። ሌሎችም አገሮችም መላእክት ያላቸው ይመስላል (ዳን. 10፡21)። በፍጻ ዘመን በአሕዛብ ላይ ፍርድን ለማስፈጸም በግልጥ ይሳተፋሉ (ራእይ 8፡9፥ 16)።

*ለማያምኑ ሰዎች የሚሰጡት አገልግሎት።* ሄሮድስ በታበየ ጊዜ በሞት የቀጣው መልአክ ነበር (ሐዋ. 12፡23)። በመጨረሻ ዘመንም ጻድቃንን ከኃጥአን የሚለዩ መላእክት ናቸው (ማቴ. 13፡39)።

እነዚህ መልካሞቹ መላእክት ከሚያከናውኗቸው *ሥራዎች* ጥቂቶቹ ናቸው። በኋላ እንደምናየው እርኩሳን መላእክትም በሰዎችና በዓለም ጉዳይ ጣልቃ ይገባሉ። እርግጥ እግዚአብሔር ዕቅዱን ለመፈጸም መላእክት ባላስፈለጉት ነበር፤ ነገር ግን እርሱ ራሱ መርጧል። ይህ በመሆኑ ግን መላእክትን እናመልካቸውም። ይህም ማለት መላእክትንም ሆነ እግዚአብሔር እቅዱን ለማስፈጸም የሚጠቀምባቸውን ሁኔታዎችና ጓደኞቹን ማምለክ አለብን ማለት አይደለም። ነገር ግን እግዚአብሔር የመረጣቸው መሆናቸውን ማጤንና ስለ እነርሱም እግዚአብሔርን ማመስገን አለብን። በስኮትላንድ በሚገኝ አንድ ጥንታዊ ቤተ ክርስቲያን ግድግዳ ላይ፥ ይህን ጉዳይ ሚዛናዊ የሚያደርግና "የእግዚአብሔር ኃይል ሊገዛን በቂ ሆኖ ሳለ፥ ደካሞች ከመሆናችን የተነሳ ግን መላእክቱን ጠባቂ አደረገልን" የሚል ጽሑፍ ተቀርፆ ይገኛል።

## ስለ ሰይጣን ትምህርት

### *ሰይጣን አለን?*

ስለ መላእክት ሕልውና መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን ለማይቀበል ሰው፥ የሰይጣንን መኖር ማረጋገጡ የዚያኑ ያህል ያስቸግር ይሆናል። ማስረጃው ግን አይገድም፤ የተትረፈረፈ ነው። 1. በስፋት ተገልጧል (ቢያንስ በብሉይ ኪዳን

ሰባት መጻሕፍትና በአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች ሁሉ ተጠቅሷል)። 2. በራሱ በክርስቶስ ቃል ላይ የተመሠረተ ነው (ማቴ. 13፥39፤ ሉቃስ 10፥18፤ 11፥18)። ክርስቶስ እነዚህን ቃላት የተናገረው የእምነት መሀይምናን ለሆኑ ሰዎች እንዳልሆነ ከነበረው ሁኔታ እንረዳለን።

## *ሰይጣን ምን ይመስላል?*

*ሰይጣን አካል ያለው ፍጡር ነው።* ሰይጣን በእርግጥ እውቀት እንዳለው (2ኛ ቆሮ. 11፥3)፥ ስሜት እንዳለው (ራእይ 12፥17)፥ ፈቃድ እንዳለው (2ኛ ጢሞ. 2፥26) ላይ ተጠቅሷል። በእግዚአብሔር ዘንድም አካል እንዳለው ፍጥረት እና ለሚያደርገው ተግባርም ተጠያቂ እንደሚሆን እንጂ፥ እንደ ግዑዝ ነገር አይደለም የሚታየው (ማቴ. 25፥41)።

*ሰይጣን ፍጡር እንጂ ፈጣሪ አይደለም (ሕዝ. 28፥14)።* ስለሆነም እግዚአብሔር ብቻ ያለው ባሕርይ፥ ለምሳሌ በሁሉ ስፍራ የመገኘት፥ ሁሉን የማወቅ፥ ሁሉን የማድረግ ተፈጥሮ የለውም። ውሱን ተፈጥሮ ነው ያለው። ያም ሆኖ ተፈጥሮው ከሰው ይልቃል። ፍጡር በመሆኑም ፈጣሪ ውሱን ሊያደርገው እንደሚችልና እንዳደረገውም በተደጋጋሚ ታይቷል (ኢዮብ 1፥12)።

*ሰይጣን መንፈስ የሆነ ፍጡር ነው።* ኪሩቤል ከተባሉት የመላእክት ወገን ነበር (ኤፌ. 6፥11-12፤ ሕዝ. 28፥14)። ከተፈጠሩት መላእክት ሁሉ ከፍተኛው ነበር (ሕዝ. 28፥12)፤ ይህም በመሆኑ ከውድቀቱ በኋላ እንኳን ከፍተኛ ኃይል አለው ("የዚህ ዓለም አምላክ"፥ 2ኛ ቆሮ. 4፥4፥ ተብሎ መጠራቱንና፥ "በአየር ላይ ሥልጣን እንዳለው አለቃ" መባሉን፥ ኤፌ. 2፥2 ያስተውሉ)።

*ሰይጣን የእግዚአብሔርና የሕዝብ ጠላት ነው።* የስሙ ትርጉም ራሱ ባላጋራ ማለት ነው (1ኛ ጴጥ. 5፥8)። ዲያቢሎስ ማለት ደግሞ ከሳሽ ማለት ነው (ራእይ 12፥10)። ዕኩይ ባሕርያቱ በመጽሐፍ ቅዱስ በተለያዩ ቦታዎች በተጠቀሱት ስሞቹ ተገልጠዋል። ክፉ (1ኛ ዮሐ. 5፥19)፥ ፈታኝ (1ኛ ተሰ. 3፥5)፥ ነፍሰ ገዳይ (ዮሐ. 8፥44)፥ ሐሰተኛ (ዮሐ. 8፥44)፤ የታወቀ ኃጢአተኛ (1ኛ ዮሐ. 3፥8) የሚሉ ስያሜዎች ተሰጥተውታል። የጠላትነት ተግባሩን ለማከናወንም በእባብ መልክ (ራእይ 12፥9)፥ በቁጣ ዘንዶ መልክ (ራእይ 12፥3)፥ በሚማርክ የብርሃን መልአክ አምሳያ (2ኛ ቆሮ. 11፥14) ይታያል። እነዚህን ሁሉ ችሎታዎቹን ለዕቅዱ ማከናወኛ በማታለያነት ይጠቀምባቸዋል።

## *የሰይጣን ኃጢአት ምን ነበር?*

ሰይጣን ኃጢአት የፈጸመው ክብርና ሥልጣን በነበረው ወቅት ነው። ኃጢአት ከማድረጉ በፊት የእግዚአብሔር በረከት ተሳታፊ ነበር። ሕዝቅኤል

28፡11-15 ሰይጣን ኃጢአትን ሲፈጽም የነበረበትን አስደናቂ የክብር ስፍራ ይገልጥልናል። የምንባቡ ክፍል የሚያስረዳው ስለ ሰይጣን እንጂ፥ ከአሕዛብ ስለፈለቀና የተጋነነ የምሥራቃውያን አፈ ታሪክ ወይም ተረት እንዳልሆነ ግልጥ ከሆኑት ቃላቱ መረዳት ይቻላል። ሕዝቅኤል የጢሮስ ንጉሥ በተለያየ መንገድ የቀዳውን የሰይጣን የተንኮል ሥራ እና እንቅስቃሴ ነበር ያየው።[1] ሰይጣን ከነበሩት መብቶች መካከል፡- 1. የላቀ ጥበብ (ቁ. 2)፥ 2. ፍጹም ውበት (ቁ. 2)፥ 3. ያማረ መልክ (ቁ. 3)፥ 4. እንደተቀባ ኪሩብ በመሆን የእግዚአብሔርን ዙፋን በመሸፈን ልዩ ስፍራ ማግኘቱ ይገኙበት ነበር። የተቀባ ኪሩብ (ቁ. 14) መሆኑም ዋናው ነገር ነበር። ቁጥር 15 ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ኃጢአት መነሻ የሚገልጠውን በመጥቀስ "በደል እስከተገኘብህ ድረስ" በማለት ይናገራል። ይህ አባባል ሰይጣን ፍጹም ሆኖ የተፈጠረ እንደነበር ያመለክታል። ለውድቀቱ መነሻ የሆነውን ኃጢአት እንዲሠራ እግዚአብሔር አላስገደደውም፤ በራሱ ፈቃድ ለፈጸመው ድርጊት ሙሉ በሙሉ ተጠያቂ ነው። ምክንያቱም ከተሰጠው ሥልጣንና መብት አኳያ ሲታይ ኃጢአት የፈጸመው በሙሉ እውቀቱ እንደሆነ ግልጥ ነውና።

የሰይጣን ኃጢአት ትዕቢት ነበር (1ኛ ጢሞ. 3፡6)። ይህ ትዕቢት እንዴት እንደገነፈለ በኢሳይያስ 14፡13-14 በዝርዝር የተገለጠ ሲሆን፥ "በልዑል እመስላለሁ" (ቁ. 14) ማለቱ ትዕቢቱን ያጎላዋል።

## *ሰይጣን ተፈርዶበታል፥ ወይስ ገና ይፈረድበታል?*

ሰይጣን ተፈርዶበታል፥ እንደገናም ይፈረድበታል። የተወሰኑበት ወይም የሚወሰኑበት ስድስት ፍርዶች አሉ። 1. ከሰማያዊ ማዕረጉ ተሽሯል (ሕዝ. 28፡16)፤ 2. አዳምንና ሔዋንን ከፈተነ በኋላ ተፈርዶበታል (ዘፍጥ. 3፡14-15)፤ 3. ማዕከላዊው ፍርድ የተከናወነው (የሌሎቹም ፍርዶች መሠረት ነውና) በመስቀል ላይ ነበር (ዮሐ. 12፡31)፤ 4. በፍዳ ዘመን ወደ ሰማይ ከመውጣት ይታገዳል (ራእይ 12፡13)፤ 5. በሺህ ዓመቱ ግዛት መጀመሪያ ላይ ታሥሮ በጥልቁ ውስጥ ይጣላል (ራእይ 20፡2)፤ 6. በሺህ ዓመቱ አገዛዝ መጨረሻ ለዘላለም ወደ እሳት ባሕር ይጣላል (ራእይ 20፡10)።

## *ሰይጣን ምን ያደርጋል?*

የሰይጣን ዓላማ በየትኛውም ቦታና በማንኛውም መንገድ የእግዚአብሔርን ዕቅድ ማጣመም ወይም ማደናቀፍ ነው። ይህን ለማከናወንም አለቃ በሆነበት ዓለም የራሱን ሥርዓት መሥርቶ የእግዚአብሔርን ገዥነት ለመቃወምና ለመቀናቀን ይጥራል። ይህን የሚያደርገው ግልጥና ተቃራኒ የሆነ መንግሥት በማቋቋም ሳይሆን፥ የእግዚአብሔርን ዕቅድ በማስመሰል ነው።

1. በክርስቶስ የቤዛነት ተግባር ወቅት በመስቀሉ ላይ ሳይሰቃይ ቤዛ የሚሆንበትን አማራጭ በማቅረብ ጌታን ፈተነው (ማቴ. 4፡1-11 እንዲሁም ማቴ. 2፡16፥ ዮሐ. 8፡44፥ ማር. 16፡23 እና ዮሐ. 13፡27 ላይ የክርስቶስን ዓላማ ለማክሸፍ ያደረጋቸውን ሙከራዎች ይመልከቱ)።

2. የዓለም መንግሥታትን በተመለከተ፥ እግዚአብሔር ብቻ የሚያደርገውን እነርሱም ማድረግ እንደማይሳናቸው በማሳየት ያታልላቸዋል (ራእይ 20፡3)። በፍጻ ዘመን መጨረሻ ላይም ወደ አርማጌዶን ለጦርነት ያስከትታቸዋል (ራእይ 16፡13-14)።

3. የማያምኑ ወገኖች ወንጌልን እንዳይቀበሉ አእምሯቸውን ያሳውረዋል (2ኛ ቆሮ. 4፡4)። ይህን የሚያደርገው ማንኛውም መንገድ ወደ መንግሥተ ሰማያት ያደርሳል የሚለውን አሳብ በማሳየት ነው። የእግዚአብሔር ቃል ሲዘራም፥ እያደባ ከሰዎች ልብ ይለቅማል (ሉቃስ 8፡12)።

4. እንዲዋሽ አማኙን ይፈትነዋል (ሐዋ. 5፡3)። በሐሰት ይከሰዋል (ራእይ 12፡10)፤ ለእግዚአብሔር እንዳይሠራ ያደናቅፈዋል (1ኛ ተሰ. 2፡18)፤ ክርስቲያንን ለማሸነፍ በአጋንንቱ ይጠቀማል (ኤፌ. 6፡11-12)፤ በኃጢአት እንዲወድቅ ይፈትነዋል (1ኛ ቆሮ. 7፡5)፤ አማኞችን ለማታለል መካከላቸው እንክርዳድ ይዘራል (ማቴ. 13፡38-39)፤ አንዳንዴም ስደት ያስነሳባቸዋል (ራእይ 2፡10)። ከነዚህ ሌላ ክርስቲያን እውነተኛውን የእግዚአብሔር ፈቃድ ትቶ አስመሳይ ዕቅድ እንዲከተል ያደርገዋል። የሚቻል ከሆነም ማታለሉ እንዳይነቃበት "ደግ" ማድረግን ይጨምራል (ፍጹም መልካሙን አይደለም)። ሆኖም አንዳንዴ ዕኩይ ተግባራትን ያከናውናል።

## አማኝ ከሰይጣን ጥቃት ራሱን የሚከላከለው እንዴት ነው?

1. አዲስ ኪዳን፥ ሁለት ቦታዎች ላይ ጌታ በሰማይ ሆኖ ለሕዝቡ እንደሚማልድ ይናገራል (ሮሜ 8፡34፤ ዕብ. 7፡25)። ይህ ምልጃ አብ ልጆቹን ከክፉ ሁሉ እንዲጠብቅለት መጠየቅን ይጨምራል (ዮሐ. 17፡15)።

2. እግዚአብሔር አንዳንዴ ለአማኙ የተለየ ትምህርት ለመስጠት በሰይጣን እንደሚጠቀምም ማስተዋል ያስፈልጋል። ይህ ሲሆን የክርስቲያኑ መከላከያ እግዚአብሔር የሚያስተምረውን በሚገባ መረዳት ይሆናል። ይህ ነበር በኢዮብና በጳውሎስ የደረሰው (2ኛ ቆሮ. 12፡7-10)።

3. ስለ ሰይጣን ተገቢ የሆነ አመለካከት ሊኖረን ይገባል። የእግዚአብሔር ኃይል ከእኛ ወገን ቢሆንም፥ ወዲያውኑ ድል እናገኛለን ብሎ

ማሰብ ብልህነት አይደለም። የሰይጣንን ኃይል አቃለው አይናገሩ፥ ይልቁንም በጌታ ድል መታመንን ይማሩ (ይሁዳ 8-9)።

4. አማኝ ስለ ሰይጣን አሠራር ማወቅ አለበት፥ መጠንቀቅም ይገባዋል (1ኛ ጴጥ. 5፡8)።

5. ቆራጥ አቋም ሊኖረው ይገባል (ያዕ. 4፥7)፤ ይህን አቋም በጠላታችን ላይ ለምናደርገው ቀጣይ ጦርነት እንደ ውጊያ ምሽግ ልንጠቀምበት ይገባል።

6. እግዚአብሔር መከላከያ የጦር ዕቃ ሰጥቶናል (ኤፌ. 6፡11-18)። እያንዳንዱ ትጥቅ በጣም ጠቃሚና ለተለየ ዓላማ የሚውል ነው። ስለዚህ በተሰጠን የጦር ዕቃ በመጠቀም ራሳችንን መከላከል አለብን።

# ስለ አጋንንት ትምህርት

## *አጋንንት ምንድናቸው?*

የአጋንንትን አመጣጥ አስመልክቶ ከክርስቲያኖችም ሆነ ከአሕዛብ ለዘመናት የተለያዩ መላምቶች ተሰንዝረዋል። ግሪኮች በሞት የተለዩ ክፉ ሰዎች ነፍሳት ናቸው ብለዋቸዋል። አንዳንድ ክርስቲያን ጸሐፊዎች ደግሞ አጋንንት ከአዳም በፊት ከነበሩ ዝርያዎች የወጡ መናፍስት ናቸው ይላሉ። ይህ አሳብ መጽሐፍ ቅዱስን የሚቃረን ባይሆንም፥ በመጽሐፉ ግን አይደገፍም፤ ስለ እነዚህ ዝርያዎች የሚነግረን አንዳችም ነገር የለም። ነገር ግን ድጋፍ ያልተለየው ሌላ አስተያየት አለ። ይህም፥ አጋንንት አለቃቸው ተብሎ ከተጠራው ሰይጣን ጋር የወደቁ መላእክት ናቸው የሚል ነው (ማቴ. 12፡24)። በዚሁ መሠረት ሁለት ዓይነት የወደቁ መላእክት እንዳሉ ከመጽሐፍ ቅዱስ በግልጥ እንረዳለን። እነዚህም በአንድ ወገን ያሉት እግዚአብሔርንና ሕዝቡን እስከተወሰነ ደረጃ ለመቃወም ነጻነት ያላቸው ሲሆኑ፥ ሌሎቹ ደግሞ በእሥር ያሉ ናቸው (2ኛ ጴጥ. 2፡4፤ ይሁዳ 6)። ምንም እንኳ እነዚህ በሁለተኛው ወገን ያሉት ለምን ታሠሩ? የሚለው ጥያቄ ክርክር (አስፈላጊ ያልሆነ ንትርክ) ቢያስከትልም፥ በዘፍጥረት 6፡2-4 ላይ የተጠቀሰውን ተፈጥሯዊ ያልሆነ ኃጢአት ስለሠሩ ሳይሆን እንደማይቀር ይገመታል። ነጻ ሆነው ከሚንቀሳቀሱት አጋንንትም እንኳን አንዳንዶቹ በታሪክ ውስጥ ለተወሰነ ዘመን ብቻ ከታዩ በኋላ የደረሱበት አለመታወቁ ይነገራል (ራእይ 9፡14፥ 16፡14)። በበኩሌ ስለ አጋንንት ያለኝ አመለካከት እንደሚከተለው ነው።




## *አጋንንት ምን ይመስላሉ?*

አጋንንት አፈጣጠራቸው እንደ መላእክት ሲሆን፥ ባሕርያቸውም ተመሳሳይ ነው። መንፈስ የሆኑ ፍጡራን መሆናቸው ቢታመንበትም፥ ሥልጣናቸው የተገደበ ስለሆነ፥ በሁሉም ቦታ ለመገኘት አይችሉም። በአንድ ጊዜ በአንድ ቦታ ብቻ ለመወሰን ይገደዳሉ። በማቴዎስ 17፡18 ላይ አጋንንት የተባለው በማርቆስ 9፡25 ላይ እርኩስ መንፈስ መባሉን ያስተውሉ።

አጋንንት እንደ መላእክትና ሰይጣን ትልቅ እውቀት እንዳላቸው ይታያል። መጽሐፍ ቅዱስ አጋንንት ኢየሱስን እንዳወቁት ይገልጣል (ማር. 1፡24)። ፍጻሜያቸው ፍዳ መሆኑና (ማቴ. 8፡29)፤ የደኅንነት ዕቅድ መኖሩንም ቀደም ሲል ያውቁታል (ያዕ. 2፡19)። እንዲሁም የተደራጀና እየተስፋፋ የሚሄድ ትምህርት እንዳላቸው እናያለን (1ኛ ጢሞ. 4፡1-3) ። በተለይ በቤተ ክርስቲያን ዘመን ማብቂያ ላይ ማታለያ ትምህርታቸው እያደገና እየተጠናከረ ይሄዳል።

## *አጋንንት ምን ያደርጋሉ?*

በአጠቃላይ አጋንንት እንደ ሰይጣን በተቻላቸው ሁሉ የእግዚአብሔርን ዓላማ ለማጣመም ይጥራሉ (ዳን. 10፡10-14፥ ራእይ 16፡13-16)። ይህን በማድረግ ነው የሰይጣንን ሥራ የሚያስፋፉት። በሰይጣን ሥር ያሉ አጋንንት ቁጥር እጅግ ብዙ ስለሆነና የማሳሳት ተልእኳቸውን ለማሳካት በየአቅጣጫው ስለሚሰማሩ፥ ሰይጣን በእንቅስቃሴው ውሱን ቢሆንም በሁሉም ቦታ የሚገኝ ያስመስሉለታል።

አጋንንት ሰዎችን በተለይ በበሽታ ያጠቃሉ (ማቴ. 9፡33፤ ሉቃስ 13፡11፥ 16)፥ በእንስሳት ውስጥ ያድራሉ (ማር. 5፡13)፥ የሐሰት ትምህርት

ያስፋፋሉ (1ኛ ጢሞ. 4፡1)። እግዚአብሔር አንዳንድ ጊዜ ዕቅዱን ለማከናወን በአጋንንት ሲጠቀም እንመለከታለን (1ኛ ሳሙ. 16፡14፤ 2ኛ ቆሮ. 12፡7)። ይህም የሚያስገነዝበን እነዚህ ፍጥረታት በእግዚአብሔር ፍጹም ቁጥጥር ሥር መሆናቸውን ነው)።

አጋንንት በመንግሥታት ጉዳይም ጣልቃ የሚገቡ ይመስላሉ። በዳንኤል 10፡13 "የፋርስ መንግሥት አለቃ" የሚለው ለዳንኤል መልስ ይዞ የመጣውን መልአክ የተቃወመውን መንፈሳዊ አካል ሳይሆን አይቀርም። ይህን መንፈስ ሊቋቋመው የቻለው ሊቀ መላእክት ሚካኤል መሆኑም ለአጋንንት እጅግ ኃይለኛነት ማስረጃ ነው። በባቢሎንና በጢሮስ መንግሥታት ጀርባም የዚህ ዓይነት የክፋት ኃይል እንዳለ ታይቷል (ኢሳ. 14፤ ሕዝ. 28)። ክፉ መናፍስት መንግሥታትን እንደሚያታልሉ በዮሐንስ ራእይም ተጠቅሷል (ራእይ 16፡13-14)። በኢሳይያስ 24፡21 ላይ እግዚአብሔር በመጨረሻ "በከፍታ ላይ ያለውን ሠራዊት በከፍታ ላይ፥ በምድርም ያሉትን ነገሥታት በምድር ላይ" እንደሚቀጣቸው ያመለክታል። ከነዚህ ጥቅሶች የምንረዳው ነገር ቢኖር፥ በተዘዋዋሪ መንገድ የምድር ነገሥታትን የሚያሳትፍ አጠቃላይ ጦርነት እንደሚካሄድና አንዳንድ አጋንንት የመንግሥታትን ጉዳይ እስከመምራት ድረስ ኃይል የሚኖራቸው መሆኑን ነው። አጋንንት በዓለም አቀፍ ጉዳዮች ላይ ያላቸውን ሚና መለየቱ ቢያዳግትም፥ ዛሬም ቢሆን ተጽእኖ እንደሚያደርጉ ግልጥ ነው።

## በአጋንንት መያዝ የሚባል ነገር አለ?

በአጋንንት የመያዝ ጉዳይ ትኩረትን የሚሻው፥ ቀደም ሲል የተረጋገጠና አሁንም ያለ በመሆኑ ስለሆነ ብቻ ሳይሆን ጌታም እርግጠኝነቱን የተናገረ ስለሆነ ነው።

እርሱም ሆነ ደቀ መዛሙርቱ እጅ በመጫንና ዘይት በመቀባት፥ በሚፈወሰው አካላዊ በሽታና በአጋንንት ደዌ መካከል ያለውን ልዩነት ተረድተው ነበር። በአጋንንት የተያዘን በሽተኛ ለማዳን፥ ከበሽተኛው ለቆ እንዲወጣ አጋንንቱን ማዘዝ ያስፈልግ ነበር (ማቴ. 10፡8፥ ማር. 6፡13)።

በአጋንንት መያዝን የመለየት ብቸኛ መንገድ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በግልጥ የታወቁ በአጋንንት የመያዝ ምሳሌዎች ላይ የተጠቀሱትን ባሕርያት መመልከት ነው። ይህ ካልሆነ ምልክቱ ማንኛውንም ሕመም ስለሚመስል መለየቱ ያስቸግራል (ማቴ. 9፡32-33)። ያም ሆነ ይህ፥ በአጋንንት መያዝ ማለት፥ አጋንንት በሰው ውስጥ በማደር የሰውየውን አእምሮ ወይም አካል በቀጥታ ቁጥጥራቸው ሥር ማድረግ ማለት ነው።

በአጋንንት መያዝንና በአጋንንት ተጽዕኖ ሥር መውደቅን መለየት መቻል እጅግ ወሳኝ ነው። አጋንንት ሥራውን የሚሠራው በተያዘው ሰው ውስጥ በመዋሃድ ሲሆን፥ ተጽዕኖው ሥር መውደቅ ግን፥ አጋንንቱ ከሰውየው ውጭ በመሆን ተጽዕኖ ሲያደርስበት ነው። ይህ ነው ዋናው ልዩነት። እርግጥ ከውስጥም ሆነ ከውጭ በአጋንንት የተያዘ ወይም የተለከፈ ሰው የሕመም ምልክትና ባሕርይ አንድ ዓይነት ሊሆን ይችላል። ክርስቲያንን አጋንንት ሊይዘው ይችላልን? የሚል ጥያቄ ከተነሳ መልሱ አይችልም ነው። ምክንያቱም የመንፈስ ቅዱስ በአማኙ ውስጥ መኖር አጋንንትን የመሰለ ሌላ ተቀናቃኝ መንፈስ አብሮት እዚያው እንዲኖር አይፈቅድለትም። ነገር ግን ጥያቄው ክርስቲያን በአጋንንቶች ይጠቃል ወይ? የሚል ከሆነ፥ መልሱ አዎ ነው። ጥቃቱም ልክ እንደ ማንኛውም በአጋንንት እንደተያዘ ሰው ሊሆን ይችላል። ከላይ እንደተጠቀሰው አልፎ አልፎ አካላዊ ሕመም በአጋንንት የመያዝ፥ ወይም የመከበብ ውጤት ሲሆን (ማቴ. 9፡32-33)፤ አንዳንድ ጊዜም የአእምሮ መዛባት በአጋንንት ከመለከፍ የመነጨ ይሆናል (ማቴ. 17፡15)። ይህ ግን ሁልጊዜ የሚደርስ ስላለመሆኑ ዳንኤል 4ን ይመልከቱ።

አንድ ሰው በስሜትና በአእምሮ ተረብሾ ሲታይ፥ ምክንያቱ አንድ ወይም ብዙ ነገሮች ሊሆኑ ይችላሉ። አብዛኛውን ጊዜ ግን፥ ብዙ ሆነው ነው የሚገኙት። ከዚህም የተነሳ ለችግሩ መፍትሔ ለመሻት በጣም ያስቸግራል። የህክምና እርዳታ ብቻ የሚያስፈልግበት ሁኔታ ሲኖር፥ ከዚህ ለተለየ በሽታ ግን አጋንንት ወደሚወጣበት መንፈሳዊ ስፍራ መውሰድ ያስፈልግ ይሆናል። አጋንንትን ማስወጣት የሚቻል ይሁን እንጂ፥ ተግባሩ ግን ቀላል አይደለም። ጌታ አጋንንት ከተባረሩ በኋላ፥ ከነሱ የከፉትን አጋንንት በመጨመር ወደለቀቁት ሰው እንደሚመለሱና የበለጠ አደጋ እንደሚያደርሱበት አስጠንቅቋል (ሉቃስ 11፡24-26)። አጋንንት ከአንድ ሰው እንደወጣ የሚያድርበት ሌላ ሰው መፈለጉ አይቀርም።

## *የአጋንንት ፍጻሜ*

አንዳንድ አጋንንት ለጊዜው ታሥረዋል። ለምሳሌ በክርስቶስ የሕይወት ዘመን ነጻ የነበሩት ወደ ጥልቁ ተወርውረዋል (ሉቃስ 8፡31)። አሁን የታሠሩት ደግሞ በፍዳ ዘመን ሥራቸውን እንዲያከናውኑ ይለቀቃሉ (ራእይ 9፡1-11፥ 16፡13-14)። ይሁን እንጂ፥ አጋንንት በመጨረሻ ከሰይጣን ጋር ወደ እሳት ባሕር ለዘላለም ይጣላሉ (ማቴ. 25፡41)።

# 6

# የሰው ተፈጥሮ

ሰው ምንድነው? የሚለው ጥያቄ ያለጥርጥር እጅግ መሠረታዊ የሆነ የፍልስፍናና የሥነ-መለኮት ተግባራዊ ጥያቄ ነው። ሰዎች፣ መጀመሪያ ከየት መጣን? ለምንስ መጣን? መሄጃችንስ ወዴት ይሆናል? የሚሉና ሌሎችም ተመሳሳይ ጥያቄዎች ያነሳሉ። ፍልስፍና እነዚህን ጥያቄዎች ለማጥናትና መልስ ለማግኘት በየዘመናቱ በተነሱ ፈላስፋዎቹ አማካይነት የተለያዩ ሙከራዎችን አድርጓል። የብዙዎቹን ፍልስፍናዎች የአጠናን ዘዴና መልሶቻቸውን ስናይ፣ ሰዎች ለነዚህ ጥያቄዎች እርግጠኛ መልስ ለማግኘት አለመቻላቸውን እንረዳለን። ፍልስፍና ሰዎች ስለ ሰው ያሰቡትን ሊያስተምረን ሲሞክር፣ መጽሐፍ ቅዱስ ግን የሰውን አፈጣጠር በማስመልከት በሥልጣን የተደገፈና የተሟላ ትምህርት ይሰጠናል። ለሌሎች መሠረታዊ ጥያቄዎችም አጥጋቢ መልስ አለው።

## የሰው ባሕርይ

### *ሰው ፍጡር ነው*

አንድ ሰው፣ ስለ ሰው ዘር አመጣጥ ያለው አመለካከት፣ ስለ ሰብአዊ ፍጡር የሚኖረውን እውቀትና አስተሳሰብ ይወስነዋል። ለምሳሌ ሰው በአዝጋሚ ለውጥ የመጣ ነው ብሎ ካመነ፣ የኃጢአትን አስከፊነትና የአዳኙን አስፈላጊነት ሙሉ በሙሉ ባይሰርዘው እንኳን እጅግ አቃሎ ይመለከተዋል። በሌላ በኩል ሰው በአምላክ የተፈጠረ ነው ብሎ የሚያምን ከሆነ፣ ይህ ዕንስ አሳብ ሰው ኀላፊነት አለበት የሚለውን የተያያዘ አሳብ ይይዛል። ሰው በእግዚአብሔር ከተፈጠረ፣ በፈጣሪና በፍጡሩ መካከል የበላይና የበታች ግንኙነት አለ ማለት ነው። ይህ ከሆነ እንግዲህ ሰው የራሱን ዕድል በራሱ የሚወስን አይሆንም፤ ወይም ለራሱ ተጠያቂ የሆነ የመጨረሻ ባለሥልጣንም ለመሆን አይችልም። ፍጡራን በፈጣሪያቸው ተገዢ መሆናቸውን ነው የሥነ-ፍጥረት ትምህርት የሚያመለክተው። ነገር ግን ሰው ከዝቅተኛ የሕይወት አካል በአዝጋሚ ለውጥ ከተገኘ፣ ፈጣሪ ሊጠየቅበት አይችልም ማለት ነው።

የአዝጋሚ ለውጥ ትምህርት በየደረጃው በሰፊው የሚሰጥ ስለሆነ፣ በዚህ ክፍል፣ ስለዚህ ዕንስ አሳብ ጥቂት አስተያየት መሰንዘሩ ብቻ በቂ ይሆናል። ይህ

ፅንሰ አሳብ፥ ፍጥረት ሁሉ ከመጀመሪያይቱ "ሕዋስ" ቀስ በቀስ በተፈጥሮ ሂደት የተገኘ ነው ቢልም፥ የመጀመሪያዋ ሕዋስ ከየት እንደመጣች ግን አያመለክትም። በተወሰነ ደረጃ አንዳንድ ለውጦች መኖራቸውን ማንኛውም ክርስቲያን አይክድም። ነገር ግን የአዝጋሚ ለውጥ ፅንሰ አሳብ ከዚህም የገዘፉ የለውጥ ትምህርቶችን ያካትታል። የቅርፅ፥ የዘርና፥ ሌሎች ውስጣዊና ረቂቅ ለውጦች ሁሉ ያለ ፈጣሪ ተሳትፎ ይፈጸማሉ ብሎ ያስተምራል።

እንዴት ነው ይህ መሆን የሚችለው? እንደ አዝጋሚ ለውጥ እምነት አራማጆች [Evolutionists/ኢቮሉሽኒስትስ] አባባል፥ ይህ የሚከናወነው በ"ሚዩቴሽን"* [Mutation] ነው። ጠንካራ ጠንካራዎቹ በተፈጥሮ ምርጫ እየተጠበቁ በመቆየታቸው አዲስ የዘር ዓይነት ተገኘ እንደሚሉም ማስተዋል ይጠቅማል። በሂሳብ ጥበብ ቋንቋ ቀመሩ የሚከተለውን ይመስላል፡- ሚዩቴሽን + የተፈጥሮ ምርጫ + ጊዜ = አዝጋሚ ለውጥ። አንድ ጸሐፊ ሲጽፍ፡- "ሜንድል [Mendel] በተባለ የለውጥ ተመራማሪ ለረዥም ጊዜ የታየው፥ የለውጥ ሙከራ የተመሠረተው ሕያው በሆኑት ባሕርያት ላይ ብቻ እንጂ፥ አዳዲስ ባሕርያት በመፍጠር እንዳልሆነ ነው። ፍጹም የሆኑ አዳዲስ አካላት ማግኘቱን ያረጋገጠ ሙከራም የለም። ይሁን እንጂ በአዝጋሚ ለውጥ ትምህርት የዋናዎቹን የለውጥ ደረጃዎች ክልል የሚያመለክተው በፍጥረታት ውስጥ የአዳዲስ ባሕርያት መከሰት ነው" ብሏል።[1]

ይህ መልስ ያላገኘ የአዝጋሚ ለውጥ እምነት አራማጆች መሠረታዊ ችግር ነው። እነዚህ አዳዲስ ነገሮች በምንም አኳኋን ይሁን በአዝጋሚ ለውጥ ተከስተዋል ብሎ ሜንድል ማመን አለበት። ለምሳሌ አንድ እውቅ የሰው ዘር አመጣጥ ተመራማሪ [Anthropologist/አንትሮፖሎጂስት] የጀርባ አጥንት ያላቸው ፍጥረታት፥ አጥንት ከሌላቸው በእድገት እንደተገኙ ሲጽፍ "ይህ በጣም ውስብስብ፥ ግልጥ ያልሆነና አሻሚ ጉዳይ ነው። ያም ሆነ ይህ አጥንት የሌላቸው እንስሳት በሆነ መንገድ የጀርባ አጥንት በማግኘት በኢቮሉሽን ተለውጠዋል" ብሏል።[2] ይህ የግል እምነቱ ቢሆንም፥ የአስተሳሰብ ድክመት ይታይበታል።

የቅሪት አካል ዘገባም ከዚህ በፊት ሆነዋል የሚባሉ ነገሮችን ያመለክታል። አዝጋሚ ለውጥ ትክክል ቢሆን ኖሮ፥ ለውጡ ሳይቋረጥ ከቀላል ወደ ውስብስብ የተሸጋገረበትን ሂደት ሊያመለክት ይገባ ነበር። ነገር ግን

---

* "ሚዩቴሽን" ማለት በአንድ ድንገተኛ ሁኔታ የተነሳ በፍጥረታት ሕይወት መዋለድ ላይ የሚመጣ መላምታዊና ድንገታዊ ለውጥ ነው። በዚህም ረገድ ከወላጆቻቸው የተለዩ አዳዲስ ፍጡራን የሚፈጠሩ ሲሆን፥ አዲስ የሆኑት ልጆችም እራሳቸውን እንጂ አያት ቅድመ አያቶቻቸውን የማይመስሉ ዘሮችን ይተካሉ።

በቢሊዮን ከሚቆጠሩት የታወቁ ቅሪት-አካላት ግኝቶችና በከፍተኛ የሕይወት ምድቦች መካከል ያለው ሽግግር ሆነ ተብሎ ተዘሏል! "አገናኞቹ ቀለበቶችም ከሚፈለጉበት ስፍራ ጠፍተዋል፤ ምናልባት ወደፊትም ብዙ አገናኝ ቀለበቶች ይጠፉ ይሆናል" በማለት አንድ ጸሐፊ ተናግረዋል።[3]

መጽሐፍ ቅዱስ የሰውን አፈጣጠር አስመልክቶ በዝርዝር ስላሰፈረው ጉዳይ የተለያዩ አስተሳሰቦች ቢኖሩም፥ እውነተኛዎቹ ማስረጃዎች ግን በዚሁ መጽሐፍ ውስጥ ነው በግልጥ የሚገኙት። ዋና ዋናዎቹም ማስረጃዎች የሚከተሉት ናቸው።

1. እግዚአብሔር ፈጣሪ ስለመሆኑ በዘፍጥረት ም. 1 ላይ ከአሥራ ሰባት ጊዜ በላይ ተገልጧል። እዚህ ላይ ትልቁ ጥያቄ የቱ እግዚአብሔር? የሚለው ነው። መልሱም ምዕራፉን የጻፈው ሰው፥ ሙሴ የሚያውቀው እግዚአብሔር፥ የሚል ይሆናል። ሙሴ በግሉ፥ ማንነቱን፥ ሕያውነቱን፥ ተአምራት አድራጊነቱን፥ የተረዳው አምላክ እግዚአብሔር ነው።

2. በዘፍጥረት መጽሐፍ ላይ የሰፈረው ቃል እግዚአብሔር ፍጥረታትን የፈጠረበትን ሁኔታ ይነግረናል። በዘፍጥረት 1፡1፥ 21 እና 27 ላይ ያለው ግስ፥ ታላቅ፥ አዲስና ታሪካዊ የሆነን ፍጥረት ያመለክታል። ዘፍጥረት 1፡1 ፍጥረት ከባዶ ነገር እንደጀመረ ያስተምራል፤ ከዚያ በፊት ምንም አልነበረም። በዚህ ምዕራፍ እግዚአብሔር "ሠራ"፥ "ጠራ"፥ "አዘጋጀ"፥ "አበጀ"፥ "አደረገ"፥ "ወሰደ"፥ "ተከለ"...ወዘተ. የሚሉ ግሶች ይገኛሉ። በተጨማሪም ፍጥረታት "ቀን" "በቀን" ከመጀመሪያው (1፡1) እስከ መጨረሻው (2፡1) እንደተፈጠሩ ያመለክታል።

3. የፍጥረታትን መፈጠሪያ ጊዜ በተመለከተም በዘፍጥረት የተጠቀሰ ማረጋገጫ አለ። የቀኖች ተራ በዘፍጥረት 1፡3 ይጀምራል። የነዚህን ቀኖች ትርጉም በተመለከተ አራት አመለካከቶች አሉ። በመጀመሪያ እነዚያ ቀኖች እግዚአብሔር ስለ አፈጣጠሩ ሁኔታ ለሙሴ የገለጠባቸው ናቸው የሚል ግንዛቤ አለ። እንግዲህ እነዚህ "የመግለጥ ቀናት" ናቸው እንጂ ከመፍጠር ጊዜ ጋር ግንኙነት የላቸውም። ሁለተኛ እነዚህ ቀናት ዘመናትን ነው የሚያመለክቱት (በብሉይ ኪዳን ቀን ረጅም ዘመንን ለማመልከት ተጽፏል፤ ኢዩ. 2፡31)። የምድር አፈጣጠር [Geological/ጂኦሎጂካል] ዘመናትም በቀላሉ በነዚህ ይካተታሉ። ሦስተኛዎቹ እውነተኛ ቀኖች ሲሆኑ (በ24 ሰዓት የሚለኩ) በመካከላቸው ሰፊ ክፍት ጊዜ አለ፥ ይህም የጂኦሎጂን ረጅም ዘመን ሊያጠቃልል ይችላል። አራተኛዎቹ የፀሐይ ቀኖች ይባላሉ። እነዚህ ክፍተት የሌላቸውና ተከታታይ ናቸው። ይህም አመለካከት "ምሽትና ማለዳ" በሚለው

ሐረግ ይገለጣል። በብሉይ ኪዳን ውስጥ የቁጥር ቅጽል ከ"ቀን" ጋር ሲጠቀስ ሁልጊዜ የሚያመለክተው እውነተኛውን የፀሐይ ቀን ነው። በዚህ አመለካከት መሠረት መሬት የተፈጠረችው በቅርብ ጊዜ ነው። ሰውም እንደቀሩት ምስት ግምቶች ሳይሆን፥ ከሌሎቹ ፍጥረታት በኋላ በቅርብ ጊዜ መፈጠሩን እንረዳለን።

ዘፍጥረት 1፡1 ከሌላው የምዕራፉ ክፍሎች ጋር ያለው ግንኙነትም አከራካሪ ሆኗል። አንዳንዶች ይህ ለመንደርደሪያነት ብቻ የሚያገለግል አረፍተ ነገር ነው ሲሉ፥ የቀሩት ደግሞ ቀደም ሲል ስለነበረና በኋላ ባልታወቀ ምክንያት ድምጥማጡ ስለጠፋ ፍጡር ነው የሚያወራው ይላሉ። ለዚህም የሚያቀርቡት ማስረጃ በቁጥር 2 ላይ የተጠቀሰውን ቃል ነው። ይህ ድንገተኛ የጥፋት አደጋ የተከሰተው በሰይጣን ውድቀት ነው ይላሉ። ይህ ጉዳይ ከዚህ ጥናታችን ጋር ግንኙነት ያለው አይደለም። የውድቀትንም መነሻ መግለጡ ያዳግት ይሆናል።

4. የጥፋት ውኃ ውጤት ያለጥርጥር ዛሬ የምናውቀውንም የዓለም ሁኔታ ለውጦታል፤ ስለዚህ ዓለም ከጥፋት ውኃ በፊት የነበራትን የተፈጥሮ ገጽታ ለመረዳት የጥፋት ውኃው ውጤት ሥእል በማንም አእምሮ ሊኖር ይገባል። ይህ የጥፋት ውኃ በአንድ አካባቢ የተወሰነ ቢሆን ኖሮ፥ በዚያው አካባቢ ብቻ ነበር ለውጥ ሊያመጣ የሚችለው፤ መሬትን በሙሉ የሸፈነ ከነበረ ግን ውጤቱ እጅግ የተወሳሰበና ከግምታችን በላይ አስደንጋጭ ነበር ለማለት ይቻላል። እንዲህ ዓይነቱ ሁለንተናዊ ማጥለቅለቅ በጣም ብዙ ቅሪት-አካላትን ሊተው እንደሚችል ይገመታል። ይህ ደግሞ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ የሚከናወን እንጂ፥ ጂኦሎጂያዊ ዘገባ እንደሚያመለክተው ረጅም ዓመታት የወሰደ ሂደት አይሆንም። ዓለም በሙሉ በውኃ ተጥለቅልቆ እንደነበር ማስረዳቱም ቀላል ነው። ስለ መርከቢቱም ግዝፈት በዘፍጥረት 7፡19-29 ላይ የተገለጠውን ልብ ይበሉ (ዘፍጥ. 6፡15)፤ መጥለቅለቁ የደረሰው በአንድ ክልል ብቻ ቢሆን ኖሮ፥ መርከብ አስፈላጊ ባልነበረም። ይህን የጥፋት ውኃ በ2ኛ ጴጥሮስ 3፡3-7 ላይ ማጤን ጠቃሚ ነው።[4]

5. ፍጥረት ሁሉ በእግዚአብሔር ተፈጠረ እስከተባለ ድረስ፥ ከፍጥረታት አንዳንዶቹ ቀደም ሲል ረጅም ዕድሜ ያላቸው ይመስሉ እንደነበር መገንዘብ ያስፈልጋል። በዘፍጥረት ሂደት የአዳምና ሔዋን አፈጣጠር ሲታይ ጊዜ በሚጠይቅ የእድገት ሂደት ያለፉ ይምሰል እንጂ፥ ገና ሲፈጠሩ ጎልማሳዎች ነበሩ። በኤደን የአትክልት ስፍራ ከነበሩት ዛፎች አንዳንዶቹ በጣም ትልልቆችና ረጅም ዕድሜ ያላቸው የሚመስሉ ነበሩ። ለምሳሌ ክርስቶስ በቃና ዘገሊላ የሠራው ወይን ጠጅ (ዮሐ. 2) ጣዕም የበሰለ ቢሆንም፥ በእርግጥ ዝግጅቱ ጊዜ የፈጀ እንዳልነበረ እናውቃለን። 4000 እና 5000 ሰዎች የተመገቡት ምግብ

ሁኔታም እንዲሁ ነው። ምግቡ ከደቂቃ በፊት የተሠራ ሲሆን፥ ሲበላ ግን ለብዙ ጊዜ የተሰናዳ መስሏል። እግዚአብሔር እነዚህን የመሳሰሉ ሁኔታዎች ስንት ጊዜ በፍጥረት ውስጥ እንዳከናወነ ባናውቅም፥ በአንዳንድ ሁኔታዎች ጎልተው መታየታቸው እውነት ነው።

6. እንደ ታሪክ እውነታ ሁሉ የፍጥረት ታሪክም በብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ተመዝግቦ እናገኛለን (ዘጸ. 20፡11፤ 1ኛ ዜና 1፡1፤ መዝ. 8፡3-6፤ ማቴ. 19፡4-5፤ ማር. 10፡6-7፤ ሉቃስ 3፡38፤ ሮሜ 5፡12-21፤ 1ኛ ቆሮ. 11፡9፤ 15፡22፥ 45፤ 2ኛ ቆሮ. 11፡3፤ 1ኛ ጢሞ. 2፡ 13-14ና ይሁዳ 14ን ይመልከቱ)። አንድ ሰው በአንዳንድ ምክንያቶች ሳቢያ በዘፍጥረት 1-11 ከተጻፈው እውነተኛ ታሪክ ለመሸሽ ቢሞክር እንኳን በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፉትን የፍጥረት ትምህርቶች (በተለይ የአዳምን ታሪክ) ሊያስወግድ አይችልም። ብዙዎች በዘፍጥረት ከ1-11 የሰፈረውን ታሪክ የሰው ምናባዊ ገለጣ ነው ይላሉ። እንዲያ ከሆነ ሌሎችንስ ክፍሎች እንዴት ያብራሯቸው ይሆን?

## *ሰው ባለ ብዙ ገጽ ፍጡር ነው*

በመሠረቱ ሰው፥ ቁሳዊ (አካል) እና ቁሳዊ ያልሆነ (መንፈስ ወይም ነፍስ ያለው) ፍጡር ነው። ሁለቱም አሠራሮች የእግዚአብሔር ቀጥተኛ የፈጣሪነት ሥራ ውጤቶች ናቸው (ዘፍጥ. 2፡7)። እግዚአብሔር ሰውን በመልኩና በምሳሌው ፈጠረ (ዘፍጥ. 1፡26፥ 5፡1)። ሰውን እጅግ ልዩ የሚያደርገው እግዚአብሔርን መምሰሉ ሲሆን፥ በኃጢአት ከወደቀ በኋላም ቢሆን ይህ አምሳያነቱ ሙሉ በሙሉ አልጠፋም። (1ኛ ቆሮ. 11፡7 እና ያዕ. 3፡9 ላይ የሰፈሩት ምክሮቹ ሰው የእግዚአብሔር አምሳያ መሆኑን ያረጋግጣሉ።) ያ አምሳያነት ምንድነው?

ለዚህ ጥያቄ፥ ለዘመናት የተለያዩ መልሶች ሲሰጡ ኖረዋል። ከነዚህም መልሶች ውስጥ የሰው የእግዚአብሔር አምሳያነቱ ከተፈጥሯዊ አካሉ ነው፥ ወይም ለሥነ-ምግባርና ለመንፈሳዊ ጉዳይ ባለው ችሎታ ነው (ችሎታው አሁንም ይኖረው ወይም ፈጽሞ ያጣው ይሆናል) የሚሉት ይገኙበታል። ምናልባት እውነቱ የብዙ ነገሮች ስብስብ በመሆኑ ይሆን ይሆናል። ሰው የእግዚአብሔር አምሳል በመሆኑ ምድርን የመግዛት ሥልጣንና ሥነ-ምግባር የማስከበር ኃላፊነት ተሰጥቶታል፤ በኋላም ይህን ኃላፊነት በኃጢአት የተነሳ ተነጥቋል። ከዓለም ገዥነቱ ተሽሯል፥ በሥነ-ምግባሩም ተበላሽቷል። ያም ሆኖ ከፍጥረታት ሁሉ በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረ እርሱ ብቻ መሆኑ ልዩ ያደርገዋል።

የሰው አካል (ቁሳዊው ክፍሉ) በጣም ብዙ ሥራ እንደሚያከናውን ግልጥ ነው። ማየት እንደ መስማት አይደለም። የስሜት ሥሮች አሠራር የተለያየና ራሱን የቻለ ቢሆንም፥ ከማየት፥ ከመስማትና ከሌሎቹም ስሜቶች ጋር የሚያያዝበት መንገድ ይኖራል።

ቁሳዊ ያልሆነውንም የሰው ክፍል በዚህ ሁኔታ ማየቱ ምናልባት አስፈላጊ ይሆናል። ነፍስ፥ መንፈስ፥ ልብ፥ አእምሮ፥ ፈቃድና ሕሊና ቁሳዊ ያልሆኑ የሰው አካል ክፍሎች ሲሆኑ፥ በመካከላቸው ጥርት ያለ ልዩነት መፍጠሩ ያስቸግራል። ሰውን አካል፥ ነፍስና መንፈስ ነው ማለት በጣም ማቃለል ይመስላል። ምክንያቱም ነፍስና መንፈስ የሰውን ቁሳዊ ያልሆነ ክፍል በሙሉ ካለመግለጣቸውም በላይ ልዩነታቸው ሁልጊዜ ጉልህ ባለመሆኑ ነው። ለምሳሌ እግዚአብሔርን በፍጹም ነፍስህ ውደድ ተብሏል (ማቴ. 22፡37)። እንዲሁም "ነፍስን ከሚዋጋ ሥጋዊ ምኞት" የሚል ሌላ ጥቅስ እናገኛለን (1ኛ ጴጥ. 2፡11)። መንፈስ ጌታን ሊያከብር ይችላል (ሉቃስ 1፡46-47)። እንዲሁም መንፈስ እንደ ሥጋ እንደሚረክስ (2ኛ ቆሮ. 7፡1) ተጽፏል። በአንዳንድ ሁኔታዎች መንፈስ የሰውን ከፍተኛ አካል ያመለክታል (ሰዎች ሁሉ፥ ያልዳኑትንም ጨምሮ መንፈስ አላቸው፥ 1ኛ ቆሮ. 2፡11)።

"ልብ" (ደም የሚረጨውን የውስጥ አካል ማለት አይደለም) እንዲሁ የሰውን ቁሳዊ ያልሆነ ክፍል ሁሉ የሚያጠቃልል ይመስላል። የሰው ሕይወት የእውቀት ማኅደር እንደሆነም ተገልጧል (ማቴ. 15፡19-20)፥ ስሜታዊውን ሕይወት (መዝ. 37፡4፤ ሮሜ 9፡2)፥ ፈቃዳዊውን ሕይወት (ዘዳግ. 7፡23፥ ዕብ. 4፡7)፥ መንፈሳዊውን ሕይወት (ሮሜ 10፡9-10፤ ኤፌ. 3፡17) ሁሉ ያጠቃልላል።

ሕሊና በሰው ውድቀት የተጎዳ አካል ቢሆንም፥ አማኞችንም ሆነ የማያምኑትን ሰዎች ሊመራ የሚችል ውስጣዊ ምስክር ነው። ሮሜ 2፡15 እና 1ኛ ጢሞ. 4፡2ን በመመልከት በማያምኑት ሰዎች ውስጥ የሚታየውን ሕሊና ያስተውሉ። አማኙን በተመለከተ ግን ሕሊናው ከመንግሥት (ሮሜ 13፡5)፥ ከአሠሪው (1ኛ ጴጥ. 2፡19)፥ ከወንድሞቹ (1ኛ ቆሮ. 8፡7፥ 10፥ 12) ጋር መልካም ግንኙነት እንዲኖረው ይመራዋል።

በጌታ ደኅንነት ያላገኘ ሰው አእምሮ፥ በአዲስ ኪዳን ውስጥ መልካም ያልሆነ ስም ተሰጥቶታል። የማይረባ (ሮሜ 1፡28)፥ ከንቱ (ኤፌ. 4፡17)፥ የረከሰ (ቲቶ 1፡15)፥ የጨለመ (ኤፌ. 4፡18)፥ በሰይጣን የታወረ (2ኛ ቆሮ. 4፡4) ተብሏል። ይሁን እንጂ አንድ ሰው ክርስቶስን አዳኝ አድርጎ ሲቀበል፥ ሕይወቱንም ለጌታ ሲሰጥ፥ የአእምሮ መታደስን ያገኛል (ሮሜ 12፡2)። ከዚያ

በኋላ እግዚአብሔርን መውደድ እንችላለን (ማቴ. 22፡37)፤ የጌታን ፈቃድ እንረዳለን (ኤፌ. 5፡17)፤ በማስተዋል እናመሰግነዋለን (1ኛ ቆሮ. 14፡15)።

የሰው ፈቃድ ሌላው በጣም ጠቃሚ የሆነና ቁሳዊ ያልሆነው የተፈጥሮ ክፍል ነው። ያልዳነ ሰው ፈቃድ መልካም ውጤት ይኖረው ይሆናል (ሐዋ. 27፡43)፤ የአማኞችም እንዲሁ ሊሆን ይችላል (ቲቶ 3፡8)፤ የዚህ ተቃራኒም ይሆን ይሆናል (1ኛ ጢሞ. 6፡9፤ ያዕ. 4፡4)።

እነዚህ ሁሉ ማብራሪያዎች፥ ክርስቲያን ሁለት የተለያዩ ችሎታዎች ወይም ባሕርያት እንዳሉት ያመለክታሉ። ከመዳኑ በፊት ችሎታውን የሚጠቀምበት ራሱን ለማገልገልና ለማስደሰት ነው። ይህ አሮጌ፥ ወይም የኃጢአት ባሕርይ ክፉ ለማድረግ ከመቻል አንጻር ብቻ አይደለም የሚተረጐመው። ከዚያ የላቀ ሊሆን ይችላል። ከአሮጌው ባሕርይ የመነጩ፥ ግን ያልከፉ ነገሮች አሉ። የአሮጌው ባሕርይ ዋና መለያ በድርጊቱ ሁሉ እግዚአብሔርን ማግለል ነው። በዳግም መወለድ ጊዜ እግዚአብሔርን ለማገልገል አዲስ ኃይል ወይም ባሕርይ ተሰጥቶናል (ሮሜ 6፡18-20፤ 2ኛ ጴጥ. 1፡4፤ ኤፌ. 4፡22-25ን ያጥኑ)።

አንድ ሰው ያሉት የሁለት ተቃራኒ ባሕርያት ግንኙነት በዚህ ወጣት ክርስቲያን ተገልጧል፡-

> በልቤ ውስጥ ሁለት ትላልቅ ውሻዎች አሉ። አንደኛው ጥሩ ውሻ ነው፤ ይረዳኛል፥ እንክብካቤ ያደርግልኛል፥ ይጠብቀኛል። ሌላው ውሻ መጥፎና ከሃዲ ሲሆን ሁልጊዜ ችግር ውስጥ የሚጥለኝና የሚያሳዝነኝም ነው። እነዚህ ውሻዎች እርስ በእርሳቸው ይጣላሉ። ሁሌም እየተጣሉ የበላይነትን ለማግኘት ይሞክራሉ። ነገር ግን ግናቸውም ቢሆኑ በመገዳደል ወይም አንዱ ሌላውን በማባረር ለማሸነፍ አይችሉም። ጥሩው ውሻ መጥፎውን አባርሮት ሰላም ለማግኘት ብችል እንዴት ደስ ባለኝ ነበር! ሕይወቴ በዚህ ቋሚ የሆነ ጦርነት በመሞላቱ የተረገምኩ ሆኛለሁ።
>
> አንድ ቀን መጋቢዬን ስለዚህ ጉዳይ ጠየቅሁትና በጣም ጥሩ ምክር ሰጠኝ፡- "አእምሮህ ውስጥ የምትጨምረው ነገር ሁሉ ለአንደኛው ውሻ የሚሆን ምግብ ነው። የእግዚአብሔርን ቃል ያለማቋረጥ ብታነብ፥ መልካም ነገር ብታስብ፥ እና የእግዚአብሔርን ፈቃድ ብትሻ ጥሩውን ውሻ መገብከ ማለት ነው። ነገር ግን ስለ ክፉ ነገሮችና ስለ ራስህ ብቻ ብታስብ ወይም ሰዎችን ለራስህ ጥቅም ለመጠጋት ብትሞክር የምትመግበው መጥፎውን ውሻ ይሆናል" አለኝ።
>
> ቀጥሎም "አብልጠህ የመገብከው ውሻ ይበልጥ ጠንካራ ይሆናል፤ ድልም ያገኛል" አለ።

## የሰው ውድቀት

ኃጢአት ለምን ከእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ ገባ? የሚለው ጥያቄ ሰው ሊመልሰው የማይችለው ነው። በምን አኳኋን ኃጢአት በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ እንደገባ ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ዘፍጥረት 3 ላይ ተገልጧል። ይህ ምዕራፍ የይዘቱን ታሪካዊነት ተረት፥ እውነተኛ ተረት፥ አፈ ታሪክ፥ የተቀደሰ አፈ ታሪክ፥ ወዘተ. እያሉ የሚክዱ ብዙ ነቃፊዎች አሉት። ይሁን እንጂ ታሪካዊ ያልሆነ "እውነተኛ" ባሕርይ አጥብቀው ይይዛሉ (መጨረሻው ውሸት የሆነ ታሪክ)። እንዲህ ያለውን የተዛባ ሥነ-መለኮታዊ አመለካከት የሚያሳይ አንድ ምሳሌ እነሆ፦

> ጠንካራ ወግ አጥባቂዎች ካልሆንን በዘፍጥረት 3 ላይ የተጻፈውን ታሪክ "እውነተኛ አፈ-ታሪክ" ነው እንላለን። ይህም ማለት ኤደን በካርታ ላይ ባይገኝም እንዲሁም የአዳም እውቀት ከሰው ልጅ የታሪክ ቀመር ወይም መዘከር ጋር ባይጣጣምም፥ ምዕራፉ ልክ በሰው ልጅ የታሪክ ጅማሬ ወቅት እንደነበረው ዛሬ ያለውን የሰው ልጅ የኑሮ ልምድ ስፋት ያሳያል ማለት ነው። በቀላል ቋንቋ ለመናገር፥ እኛ የወደቅን ፍጡሮች ነን፤ የአዳምና የሔዋን ታሪክም የኔና የእናንተ ታሪክ ነው።[5]

ይህ አባባል በዚህ መልኩ ይቅረብ እንጂ፥ የታሪኩን መዋቅር፥ ዝርዝር ሁኔታውንና ተከታታይ ጥቅሶቹን ልብ ብሎ ያጤነ፥ ታሪኩ እውነታ እንዳለው ይረዳል። (ማቴ. 19፡3-6 እና ሮሜ 5፡12-21፤ እንደዚሁም ሉቃስ 3፡38 እና ይሁዳ 14 አዳም ማለት የሰው ዘር ማለት ሳይሆን፥ አንድ ግለሰብ መሆኑን ነው የሚያመለክቱት።)

### *ፈተናው*

አዳምና ሔዋን የተፈተኑበት ሁኔታ ታላቅ ትርጉም ያለው ሲሆን፥ ባንጻሩም ቀላል ነው። ቀላልነቱም በኤደን ገነት ካሉት እጅግ ብዙ ፍሬዎች መካከል አንዱን ብቻ ከመከልከላቸው አንጻር ሲታይ ነው። ክፉን ነገር በሙከራ እንዳያውቁ መከልከላቸው የእግዚአብሔር በረከት እንጂ፥ የሕይወታቸው ጉድለት አይደለም። በሌላ አቅጣጫ ስንመለከተው ግን እገዳው የሞት ወይም የሕይወት ጉዳይ ነውና ታላቅ ጠቀሜታ ነበረው። ትእዛዙን ማክበር፥ ወይም መጣስ፥ ለእግዚአብሔር ፈቃድ መገዛትን ወይም አለመገዛትን የሚያሳይ ነበር። (እርግጥ አዳምና ሔዋን ሌላም ኀላፊነት ነበረባቸው። ለምሳሌ፦ የኤደን ገነትን

መንከባከብ።) በኋላ በግልጥ እንደሚታየው ከፉውንና መልካሙን የምታስታውቀው ዛፍ እውነተኛ ዛፍና እግዚአብሔር ይህንኑ እውቀት እንድታስተላልፍ መሳሪያ ያደረጋት ነበረች።

## *የፈተናው ሂደት*

የሰይጣን ጥቃት በማባበል የተጀመረው በዘፍጥረት 3፥1 ነው። እግዚአብሔር አንዳች ነገር እስከነፈጋቸው ድረስ ለነሱ መልካም አለመሆኑን ሔዋን እንድታምን ማድረግ ነበር የሰይጣን ሙከራ። ቁጥር 2 ላይ እንደተገለጠው የሷ መልስም እግዚአብሔር ሁሉን እንደፈቀደላቸውና አንድ ነገር መከልከሉ ቀላልና የማይጎዳቸው መሆኑን የሚገልጥ ነበር። የሰይጣን ሙከራ ሔዋን በእግዚአብሔር ቅር እንድትሰኝ ማድረግ ነበርና "እግዚአብሔር መልካም ቢሆን" ሲል ይጀምርና "አንዳችም ነገር አይከለክላችሁም ነበር። ነገር ግን የዚህን ዛፍ ፍሬ እንዳትበሉ ከልክሏልና መልካም ሊሆን አይችልም። በተቃራኒው የእኔ ዕቅድ እግዚአብሔር የከለከላችሁን ሁሉ እንድታደርጉ ይፈቅድላችኋል" የሚል ነበር ማታለያው።

የዚህ አሳብ መንደርደሪያ ነጥብ፥ የምክንያት አደራደር ቅደም ተከተልን የተከተለ ነበር። መነሻው፥ ወይም ዋናው ነጥብ እገዳ መልካም አይደለም የሚል ነው። ቀጣዩ ነጥብ የእግዚአብሔር ዕቅድ እገዳን ይደግፋል የሚል ሲሆን፥ ከዚህ በመነሳት ድምዳሜው የእግዚአብሔር ዕቅድ መልካም አይደለም፤ በተቃራኒው እገዳ የሌለው የሰይጣን ዕቅድ መልካም ነበር የሚል ሆነ።

ሔዋንም ልትፈጽመው ስለወሰነችው ስሕተት ራሷን በራሷ ትክክለኛ ለማድረግ ምክንያቶቿን በሕሊናዋ ደረደረች። የተከለከለውን ፍሬ በመመልከት፥ ለምግብነት መልካም ነው ብላ አሰበች። ደግሞም እግዚአብሔር ጣፋጭና የተለያየ ምግብ ለባሏ የማዘጋጀት ኀላፊነት እንደጣለባት በማስታወስ ይህን መልካም ፍሬ መመገብ በምንም አኳኋን ስሕተት አይሆንም ብላ አመነች። ስለ ፍሬውም ማግርና የእውቀት ምንጭነት የተለመደ ምክንያቷን አቀረበች። እግዚአብሔር ያን ፍሬ እንዳይበሉ የመከልከሉ እውነት ከአእምሮዋ ጠፋ። ድርጊቱን መልካም ለማስመሰል በምታደርገው ጥረት የተነሳ አእምሮዋ በምክንያቶች የተሞላ ስለነበር እሷና አዳም የእግዚአብሔርን ፈቃድ በግልጥ በመጣስ ከፍሬው በሉ።

## *የኃጢአታቸው ውጤቶች*

በዚህ ኃጢአት የተነሳ ቀጥሎ ያሉት ሁኔታዎች ተከሰቱ፥

1. እባብ በደረቱ እንዲሄድ ተፈረደበት (ዘፍጥ. 3፡ 14)።

2. ሰይጣን ከሴቲቱ ከሚወለደው ዘር ጋር ጠላትነት እንዲኖረውና ክርስቶስን የሚያሳምም፥ ግን ሊያጠፋ የማይችል ቁስል (በተረከዙ*) እንዲሰጠው ተፈቀደለት (ቁ. 15)። እርሱ ግን ሕይወቱን የሚያጠፋ ቁስል (በራሱ) እንዲደርስበት ተፈረደበት ("ራሱን" የሚለውን ቃል "ተረከዙን" ከሚለው ጋር ያነጻጽሩ)።

3. ሔዋንና ሴቶች ሁሉ በፅንስ ጊዜ በጭንቅ እንዲወልዱና ለባሎቻቸውም ተገዢ እንዲሆኑ ተወሰነባቸው (ቁ. 16)።

4. አዳምና ሰዎች ሁሉ በመሬት መረገም ምክንያት አድካሚ የሆነ ሥራ እንዲሠሩ ተወሰነባቸው (ቁ. 17-19)።

5. የሰው ዘር ከእግዚአብሔር ጋር የነበረው ኅብረት ተቋረጠ፤ መንፈሳዊና ሥጋዊ ሞትም መጣ፤ ከኤደንም በረከት ተከለከለ። የአዳምና የሔዋን ኃጢአት የታሪክን አቅጣጫና የእነርሱን ዘር ሕይወት ሁሉ ቀየረ (ሮሜ 5፡ 12-21ን እንደገና ያንብቡ)።

# የሰው ኃጢአት

## *የኃጢአት ትርጉም*

ኃጢአት የሚለውን ቃል ይተረጉማሉ የተባሉ ብዙ አስተሳሰቦች በየጊዜው ተሰጥተዋል፤ ትርጉሞቹም ግልጥ በሆኑ ክፍሎች ይመደባሉ።

1. አንዳንዶች፥ ኃጢአት ቅዠት ነው፥ ኃጢአት የሚባል ነገር የለም፤ በሰው ዘንድ ድክመት ቢኖርም በቂ ጊዜ ካገኘ በአዝጋሚ ለውጥ ሂደት የሚወገድ ነው ይላሉ። አንድ ሀኪም በቅርብ ጊዜ "በሥነ-አእምሮ ህክምና ኃጢአት ለሚባል አሳብ ቦታ የለንም" ብሏል። ከዓመታት በፊት ብዙ ፈላስፎች ሰው ስለ ኃጢአት የሚያስበው ከእውቀት ማነስ የተነሳ ነው፤ በቂ እውቀት በሚያካብትበት ጊዜ ግን ኃጢአት የሚባለውን ቅዠት ከአእምሮው ይፍቃል ብለዋል።

---

* በ1962 ዓ.ም. ታትሞ የወጣው የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ እባቡ የሔዋንን ዘር "ሰኰና" ይቀጠቅጠዋል በሚል የተተረጎመ ሲሆን፥ በ1988 ዓ.ም. ተሻሽሎ በታተመው መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ግን እባቡ "ተረከዙን" ይነክሰዋል በሚል ተጽፏል።

2. ኃጢአት ከእግዚአብሔር ቁጥጥር ውጭ እና ከእግዚአብሔር ነጻ የሆነ የክፋት ዘላለማዊ መመሪያ ነው የሚሉ አሉ። ይህ ሁለት አመለካከቶችን ያቀፈ ፍልስፍና [Dualism/ዱወሊዝም] ከጥንታዊው የሃይማኖት መሪ ከ"ዞርአስተር" [Zoroaster] እና ከቻይናውያኑ ከ"ያንግ" [Yang] እና "የን" [Yin] አስተሳሰብ፥ እንዲሁም ከቀድሞዎቹ ግኖስቲኮች [Gnostics/ ናስቲክስ] እምነት ጋር የተያያዘ ነው።

3. ኃጢአት ራስ ወዳድነት ነው። ይህ በብዙዎች ዘንድ የተለመደና በመጽሐፍ ቅዱስም የሚጠቀስ ይሁን እንጂ፥ ሌሎቹን የኃጢአት ምንጮች ያጠቃለለ አይደለም። በዚህ ትርጉም መሠረት ለምሳሌ:- ድሆችን ለመመገብ ከሀብታም የሚሰርቅ ሰው ድርጊት፥ ራሱን ከመውደድ የተነሳ ያልተፈጸመ ሊሆን ይችላል። ይሁን እንጂ ድርጊቱ ኃጢአት መሆኑ አያከራክርም። የአብዛኛው የኃጢአት ምንጭ ራስ ወዳድነት መሆኑ ግን አሌ የሚባል አይደለም።

4. በ1ኛ ዮሐንስ 3፡4 ላይ ለኃጢአት የተሰጠው ትርጉም ዓመፀኝነት (ከሕግ ውጭ መሆን) የሚል ነው። ይህ ቀላል ትርጉም ተጨማሪ ማብራሪያ ያስፈልገዋል። ኃጢአት ምን እንደሆነ ለማሳወቅም ሕግ ምን እንደሆነ መግለጥ አለብን። የሕግን ትርጉም ለማሳወቅ ደግሞ በየትኛው የታሪክ ዘመን ላይ ሆነን እንደምንነጋገር መገንዘባችን ወሳኝ ይሆናል። ሕግ በኤደን ገነት አንድ ነገር ማለት ሲሆን፥ ሕግ በአብርሃም ዘመን፥ እንዲሁም ሕግ በሙሴ ዘመን የተለየ ትርጉም ነበረው። ዛሬ ደግሞ ሕግ፥ በአዲስ ኪዳን የተጻፉ ብዙ ትእዛዞች ናቸው። እንግዲህ ኃጢአት እነዚህን ትእዛዞች መጣስ ነው። ቁልጭ ያለ ማብራሪያ በ1ኛ ቆሮንቶስ 10፡31 ላይ እናገኛለን። አማኞች የሚያደርጉትን ሁሉ ለእግዚአብሔር ክብር እንዲያደርጉ ታዘዋል። ስለዚህ የኃጢአት አጠቃላይ ትርጉም ከእግዚአብሔር ክብር የሚያንስ ማንኛውንም ነገር መፈጸም ማለት ነው። ይህ እርግጠኛው የኃጢአት መለኪያ ስለመሆኑ በሮሜ 3፡23 ላይ ተጽፏል።

## የግል ኃጢአት

በብሉይ ኪዳን ኃጢአትን የሚገልጡ ስምንት መሠረታዊ ቃሎች ሲኖሩ፥ በአዲስ ኪዳን ደግሞ፥ ቢያንስ አሥራ ሁለት አሉ። እነርሱም የሚያመለክቱት:- 1. በግልጥ የሚታወቅና ኃጢአት የተፈጸመበት መመዘኛ ሁሌ ይኖራል፤ 2. ክፋት የተለያዩ ቅርፆች ሊኖሩት ይችላል፤ 3. የሰው ኀላፊነት ግልጥና የማያሻማ ነው፤ 4. ኃጢአት በእግዚአብሔር ላይ ማመፅ ነው። ለዚህ የሚረዱ ጥቅሶች፥ ዘፍጥ. 38፡7፤ ሕዝ. 48፡11፤ 1ኛ ነገሥ. 8፡50፤ ማቴ. 5፡21፤ 1ኛ ቆሮ. 6፡9፤ ገላ. 6፡1፤ 1ኛ ጢሞ. 4፡2 ናቸው። የግል ኃጢአት ማለት ዒላማን መሳት ማለት ብቻ አይደለም፤ እግዚአብሔር ያቀደልንን ዓላማዎችና ግቦችን አለሟሟላት ማለትም ነው።

## የኃጢአታዊ ተፈጥሮ ውርስ

ከፍጥረታችን የቁጣ ልጆች እንደሆንን ሐዋርያው ጳውሎስ ይገልጣል (ኤፌ. 2፡3)። ይህ ኃጢአታዊ ተፈጥሮ፥ ሰዎች ሁሉ በትውልድ የወረሱት በእግዚአብሔር ዘንድ የማያስመሰግን መልካም፥ ክፉ ወይም ገለልተኛ ነገር የማድረግ ችሎታ ነው። የሰው ባሕርይ በየአቅጣጫው እንደተበላሸ የሚነግሩን ብዙ ጥቅሶች በመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ውስጥ አሉ። አእምሮው (2ኛ ቆሮ. 4፡4፤ ሮሜ 1፡28)፥ ሕሊናው (1ኛ ጢሞ. 4፡2)፥ ፈቃዱ (ሮሜ 1፡ 28)፥ ልቡናው (ኤፌ. 4፡18)፥ ሁለንተናው (ሮሜ 1፡18-3፡20) ሁሉ ተበላሽቷል። ይህ የአጠቃላይ ኀዶሎነት [Total Depravity/ቶታል ዲፕራቪቲ] ትምህርት ይባላል። አጠቃላይ ኀዶሎነት ሲባል ሁሉም ሰው በድርጊቱ ፍጹም ኀዶሎ ሆኗል፥ ወይም ሁሉም በማንኛውም ዓይነት ኃጢአት ውስጥ ይዘፈቃል፥ ወይም አንድ ሰው በጎ ድርጊትን አይወድም እንዲሁም አያደርግም ማለት አይደለም። ለማለት የተፈለገው፥ ኃጢአት የሰዎችን ሁለንተና እንደሚበክል፤ በዚህም የተነሳ፥ ተፈጥሯዊ ሰው በእግዚአብሔር ፊት ዋጋ የሚያስገኝለትን ነገር እንደሚያጣ ነው።

## የኃጢአት ብክለት [Imputation/ኢምፒዩቴሽን]

የሥነ-መለኮት ምሁራን የኃጢአትን ብክለት በተመለከተ ብዙ ተከራክረዋል። ብዙዎች የአዳም ኃጢአት ከርሱ በኋላ በተወለዱት ሁሉ ላይ ተላልፏል ሲሉ፤ ሌሎች ደግሞ አዳም የሰውን ልጅ ወክሎ ቢያጠፋም፥ የርሱ ኃጢአት ወደ ሌሎቹ አይተላለፍም ይላሉ። ይህ ሁሉ ክርክር፥ የሮሜ 5፡12ን ትርጉም መነሻ በማድረግ ሲሆን፤ በተለይ "ሁሉ ኃጢአትን አደረጉ" የሚሉትን ቃላት በተመለከተ ነው። የቃላቱ ትርጉም ሰዎች ሁሉ ኃጢአተኞች ናቸው ማለት ነው (ኃጢአታዊ ተፈጥሮ አላቸው ማለት ይሆናል)? ወይስ አዳም ኃጢአት በፈጸመ ጊዜ በአንዳች ሁኔታ የሰው ዘሮች ሁሉ ኃጢአት ሠሩ ማለት? ሁለተኛው አስተሳሰብ እውነት ከሆነ፥ የኃጢአትን ብክለት ያመለክታል።

ብዙዎች ይህን አሳብ ልክ አይደለም፥ ምክንያቱም አንድ ሰው ገና ሳይወለድ ለተሠራው ኃጢአት እንዴት ጥፋተኛ ይሆናል? ይላሉ። መደምደሚያው ትክክል ቢሆንም ባይሆንም፥ ይህ አሳብ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥም ሆነ ውጭ ያለ መሆኑ ግልጥ ነው። (ከመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ውስጥ 1ኛ ሳሙ. 22፡15፤ 2ኛ ቆሮ. 5፡21፤ ዕብ. 7፡9-10ን እንደ ምሳሌ ይመልከቱ።) ለምሳሌ:- የሌባ ወይም የነፍሰ ገዳይ ልጆች ምንም እንኳን ወላጆቻቸው ወንጀሉን በፈጸመበት ጊዜ ሕፃናት ቢሆኑና ስለ ወንጀሉም ምንም

የማያውቁ ቢሆኑም እድሜ ልካቸውን በእፍረትና በስቃይ እንደሚኖሩ ይታወቃል።

(በሌላ በኩል አንዳንድ ሰዎች ሌሎች በሠሩት ሥራ ሲጠቀሙና የማይገባቸውን ነገር ሲያገኙ ይታያል። ለምሳሌ ያህል ገና ያልተወለዱ ልጆች እንኳን ስለ ውርስ ጉዳይ በፍርድ ቤት በሚሰጡ ውሳኔዎች ምክንያት ብዙ ጊዜ ጥቅም ያገኛሉ።)

በኃጢአት የመበከል አሳብ በመጽሐፍ ቅዱስ የተረጋገጠ ከሆነ (ይመስላልም)፥ ከዚህ ጋር ሰው በግሉ የሚሠራው ኃጢአት፥ የተፈጥሮ ደካማነቱ፥ እነዚህ ሦስቱ አንድ ላይ ተዳምረው ነው እግዚአብሔር በሰዎች ኃጢአት ላይ እንዲፈርድ ምክንያት የሚሆኑት።

## ኃጢአትና ክርስቲያን

*የኃጢአት እርግጠኛነት።* ክርስቲያን መሆን አንድን ሰው ኃጢአት ከመሥራት ነጻ አያደርገውም። እርግጥ በምድራዊ ሕይወቱም ቢሆን ክርስቲያን ከኃጢአት ባሕርያት የነጻ ሊሆን ይችላል ብለው የሚያስተምሩ አሉ። የአዲስ ኪዳን ትምህርት ግን ከዚህ የተለየ ነው። ለማስረጃም ያህል ዮሐንስ በርሱ ዘመን የነበሩ ሰዎች በሐሰት የሚናገሯቸው ሦስት ነገሮች እንዳሉ በ1ኛ ዮሐንስ 1፡8-10 አረጋግጧል። እነዚህም ቁጥር 8 የኃጢአት መመሪያ መኖርን መካድ፥ ቁጥር 9 የተወሰነ ኃጢአትን መካድ፥ ቁጥር 10 በግል ኃጢአት ማድረግን መካድ ናቸው።

*የአማኝ ግዴታዎች።* የአማኝ ግዴታው “በብርሃን መመላለስ” ነው (1ኛ ዮሐ. 1፡7)። ኅብረትም የሚገኘው ይህ ብርሃን መልካምንና ክፉውን እንዲገልጥ በመማለድና ለዚህ ብርሃን ሳያቋርጡ ታዛዥ በመሆን ነው። ክርስቲያን በዚህ ምድራዊ አካል እስካለ ድረስ፥ ብርሃን መሆን አይችልም፤ ነገር ግን በብርሃን ለመመላለስ መቻል ይኖርበታል። ይህን ሲያደርግ ሁለት ነገሮች ይከናወናሉ። በመጀመሪያ ከሌሎች አማኞች ጋር ኅብረት ይኖረዋል፥ ሁለተኛ ይነጻል። ይህ መንጻት በብርሃን የመመላለሱ ውጤት እንጂ፥ ኃጢአትን የመናዘዝ ውጤት ሊሆን አይችልም። በሌላ አነጋገር በብርሃን መመላለሳችን ድካምና ኃጢአታችንን ስለሚያሳየን፥ የማያቋርጥ መንጻት እንፈልጋለን። ይህ የሚገኘው ደግሞ በክርስቶስ ሞት በኩል ነው። በብርሃን መመላለስ የሚያስናክሉንን የሕይወት ጨለማ ጎኖች በመገንዘብ ወዲያው ንስሐ እንድንገባ ያደርገናል። በዚህ ብርሃን በበለጠ መመላለሳችንም በርቀት ያለውን ጨለማ በማስወገድ፥ ከበፊቱ የበለጠ ብርሃን ያስገኝልናል። ክርስቲያኖች ሁልጊዜ ይህን ጎዳና ልንከተል ይገባል። ይህ ማንኛውም አማኝ በመንፈሳዊ ጉዞው ወቅት የሚያስፈልገው ጉዳይ ነው።

*የኃጢአት መከላከያ።* ምን ጊዜም ቢሆን በበሽታ ከመለከፍ፥ መከላከያ ክትባት መውሰድ ይመረጣል። እግዚአብሔርም ለአማኞች ኃጢአት መከላከያ አዘጋጅቷል። አንደኛው የእግዚአብሔር ቃል ነው (መዝ. 119፡11)። ሌላው የክርስቶስ የማያቋርጥ ምልጃ ነው (ዮሐ. 17፡15)። ሦስተኛው የመንፈስ ቅዱስ በክርስቲያኑ ሕይወት የሚያከናውነው አገልግሎት ነው (ዮሐ. 7፡37-39)።

*የኃጢአት ቅጣት።* 1. ማንኛውም ኃጢአት በአማኙና በሰማያዊው አባቱ መካከል ያለውን ግንኙነት ይቀንሳል (1ኛ ዮሐ. 1፡6)፤ 2. አንዳንድ ኃጢአቶች፥ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት አጥፊውን ወንድም እስከማግለል እርምጃ እንዲወስዱ የሚያደርጉ ይሆኑ ይሆናል። ያን የሚያደርጉት ግን ያ ወንድም ወደ ጌታ የሚመለስበትን ተስፋ በማሰብ ይሆናል (1ኛ ቆሮ. 5፡4-5)፤ 3. ለማያቋርጥ ኃጢአት የሚወሰኑና የተለያዩ ቅጣቶችም ይኖራሉ (ዕብ. 12፡6)፤ 4. በአንዳንድ አጋጣሚዎች፥ ከኃጢአት ያልተላቀቀን አማኝ በኃጢአት ልምዱ መከፋት የተነሳ ጌታ ወደ ሰማይ ይወስደው ይሆናል (1ኛ ቆሮ. 11፡30)።

*የኃጢአት መፍትሔ።* በማንኛውም ጊዜ ኃጢአትን ማድረጋችን ሲታወቀን በፈቃዳችን ለመናዘዝ የተዘጋጀን መሆን አለብን። በግሪክ "መናዘዝ" የሚለው ቃል አንድን ቃል መልሶ መናገርን ያመለክታል። መስማማትን፥ በሙሉ ልብ መቀበልን ያሳያል (1ኛ ዮሐ. 1፡9)። አማኝ ኃጢአቱን ሲናዘዝ፥ እግዚአብሔር ስለዚያ ኃጢአት በተናገረው ቃል መስማማቱ ነው፤ ያለፈ ስሕተቱንና ጥፋቱን ይገነዘባል። መናዘዝ ፈጣን ይቅርታ ለማግኘት የሚደረግ ማነብነብ አይደለም። ንስሐ መግባት መናዘዝንና ኃጢአት ለመተው መሻትን ያጠቃልላል (ሐዋ. 19፡18)። ይሁን እንጂ ማነው በተናዘዘበት ኃጢአት ደግሞ ደጋግሞ ያልወደቀ? ይህ ሁኔታ ቢከሰት በኑዛዜው ላይ የጎደለ ነገር መኖሩን አያመለክትም፤ ምናልባት ከንስሐ ጋር የተወሰዱት እርምጃዎች በመንፈስ ቅዱስ በመደገፍ ለድል የሚያበቁ አይደሉ ይሆናል።

በኃጢአት ምክንያት የተቋረጠው የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባልነት፥ በንስሐ ጊዜ ተመልሶ ይመሠረታል። ኃጢአት አንድን ሰው ከቤተሰብ አባልነቱ አያሰርዘውም፤ ነገር ግን የቤተሰቡን ሙሉ ደስታ ተካፋይ እንዳይሆን ያግደዋል። መናዘዝ ግንኙነቱን ያድሰዋል። በዚህ ቤተሰብ ውስጥ ያለው ዘላለማዊ ኅብረት ጨርሶ ሊበላሽ አይችልም። ነገር ግን በኃጢአት ምክንያት ሊቋረጥ ይችላል። ያንድ ሰው ኃጢአት ሌሎቹን የቤተሰብ አባላትም ሊጎዳ ስለሚችል፥ ግንኙነቶቹን ለማስተካከል ተገቢው እርምጃ ሊወሰድ ይገባዋል። ኃጢአት እጅግ ከባድ ነገር ነው፤ እግዚአብሔርን ያሳዝናል፥ ሌሎችንና እኛንም ይጎዳል።